ሰኔ 17 ቀን 2017 ዓ.ም

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2016 በጀት ዓመት ሒሳብ የፋይናንሺያል፣ የሕጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ አፈ ጉባኤ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቋ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ!

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1146/2011 አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ፣ በኢንቨስትመንት ፋይናንሲንግ የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት ተከናውኖ የቀረበ ሪፖርት ነው።

በዚህ የ2016 በጀት አመት ኦዲት የተጠቃለለ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ ኦዲት ፣ የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ ኦዲት፣ የፌዴራል

መንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት እና ከተለያዩ አካላት የተጠየቁ የልዩ ኦዲቶች፣ ሪፖርቶች ናቸው፡፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በመንግስትና የልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡
3. የ2016/17 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡
4. የ2016 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች የ163 መ/ቤቶች የፋይናንሺያልና ሕጋዊነት ኦዲቶች፣ እንዲሁም 31 አዳዲስ እና 8 ክትትል በድምሩ 39 የክዋኔ ኦዲቶች ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም የእነዚህ ሪፖርቶች ቅጅ 2 ጥራዞች/የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡
5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም በተጨማሪ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡
6. ኦዲቱ የተካሄደው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የሥጋት ደረጃ እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡ ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

I. የክትትል ኦዲት፤

1. እርምጃ ያልተወሰደባቸው በ2015 እና ከዚያ በፊት ያሉት ኦዲት ግኝቶች፤

7. በ2015 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት በተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጠቅላላ እንዲመለስ አስተያየት ከተሰጠበት ብር 20,488,520,455.02 እና በዩኤስ ዶላር 23,230.43 ውስጥ 2,914,760,469.34 (14.2%) እና በዩኤስ ዶላር 30 (0.13%) ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ብር 17,573,759,985.68 (85.8%) እና በዩኤስ ዶላር 23,200.00 (99.87) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

8. በግኝቱ ላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ ከወሰዱት መካከል በ5 የገቢዎች ሚኒስቴር ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,682,985,836.26 (ከ10% እስከ 96%)፣ በጉምሩክ ኮሚሽን በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 655,291,142.87 (ከ3% እስከ 34%)፣ የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,490,932.84 (100%)፣ የሃሮሚያ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,102,289.03 (50%) በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

2. በ2015 እና ከዚያ በፊት የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበላቸው የኦዲት ግኝቶች፤

9. በ2015 እና ከዚያ በፊት የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ለተፈጸሙ ክፍያዎች በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት የተሟላ የሰነድ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ26 መ/ቤቶች ማስረጃ ሊቀርብለት ከሚገባው በጠቅላላው ብር 3,622,741,057.36 ውስጥ ለብር 1,949,879,569.41 (54%) ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ለብር 1,672,861,487.75 (46%) ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

10. በግኝቱ ላይ እርምጃ ከወሰዱት መካከል የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 1,584,935,217.72 (99.5%)፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር ብር 136,999,117.77 (35%)፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 116,032,664.76 (97%)፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 56,178,158.97 (100%)፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,577,165.98 (44%)፣ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ብር 21,524,497.02 (90%) በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

11. በተጨማሪም በ2015/2016 በጀት አመት ተሰርተው ለመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተለይተው ከቀረቡለት የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ውስጥ 20 ይፋዊ የህዝብ ስብሰባዎችን የባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ እና 15 የመስክ ምልከታዎች አካሂዷል፡፡ በዚሁ መሰረትም ይፋዊ ውይይቱ በሚደረግበት ወቅትም የኦዲት ግኝቱን ባህሪ መነሻ በማድረግ አቅጣጫዎች የተቀመጡ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው የፌዴራል ተቋማት መካከል ነቀፌታ የሌለበት (Clean Opinion)

የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው በገንዘብ ሚኒስቴር አማካይነት በ2017 በጀት ዓመት ለ12 ተቋማት የዕውቅና እና የምስጋና ደብዳቤ ተሰጥቷል፡፡

12. በሌላ በኩል ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse or Disclaimer) የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸውን የፋይናንስ አዋጁን ተከትሎ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሰረት ተግባራዊ ያላደረጉ በ7 መ/ቤቶች በተቋሙ የበላይ አመራሮች በገንዘብ እንዲቀጡ የተደረገ ሲሆን ለተቋሞቹም ከባድ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷል፡፡

II. የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፤

1. የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን፤

13. በ2016 በጀት አመት በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ስድስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት እና በአንድ የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በአጠቃላይ በ8 ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከየካቲት 2016 እስከ ጥር 30/2017 ድረስ በ2016 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 182 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 169 መ/ቤቶችን እና 51 ቅርንጫፎች በመሥሪያቤታችን የተቀሩትን 13ቱን ለመስሪያቤታችን ተጠሪ በሆነው በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በ6 መ/ቤቶች በጸጥታ ምክንያት ኦዲቱ ያልተከናወነ ሲሆን አንድ የተጠቃለለ የመንግስት ሂሳብን ጨምሮ 163 መ/ቤቶች እና 51 ቅርንጫፎች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ ተደርጓል፡፡ በዚህም የመንግሰት ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ 96.7 ፐርሰንት መፈጸም ተችሏል።

2. በ2016 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎች ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች፤

14. የ2016 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት በ2015 እና በ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነጻጸር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ (የተሰጠው የኦዲት አስተያየት)	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2014	2015	2016
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	73	79	115
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ የሆነ አስተያየት	65	50	38
አስተያየት መስጠት ያልተቻለባቸው	6	7	0
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	20	15	10
በፀጥታ ምክንያት ኦዲቱ ያልተሰራ	1	10	6
ድምር	165	162	169

3. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ፤

3.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፤

15. ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር **3,238,356.80** የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

16. በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ እንዲተካ እንዲሁም የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጡ ሰራተኞች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.2. ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ፤

17. የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 6 አንቀጽ 34(1/ሀ) መሰረት ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም በባንክና በሳጥን የተገኘው ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ5 የጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ4 ተቋማት በጠቅላላው **40,104,982.71** ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ በባንክና በሳጥን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

18. ገንዘቡን ወደ መንግሥት ካዝና ፈሰስ ካላደረጉ ተቋማት ውስጥ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 29,702,516.95፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,465,206.60፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,602,894.02፣ ታጁራ ጉዳይ ማስፈፀሚያ ጽ/ቤት ብር 559,565.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

19. በመሆኑም ገንዘቡ ወደ መንግሥት ካዝና ፈሰስ እንዲደረግ ለወደፊቱም በመመሪያው መሰረት በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ላይ የሚደረገው ቁጥጥርና ክትትል መጠናከር እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3. ከ10 ዓመት በላይ በባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ላይ ሲንከባለል የመጣ ሂሳብ፤

20. በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት አንቀፅ 23 (3) መሰረት የባንክ የገቢና የወጪ ሂሳቦች አስፈላጊ ከሆኑ ማስረጃዎች ጋር ተገናዝበው በትክክል ተመዝግበው በሌጀር ላይ መወራረሳቸውን እንዲሁም በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እየተዘጋጀ በትክክል እየታረቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም በቀረበው የባንክ ማስታረቂያ (Bank Reconciliation Report) በባንክ ሒሳብ ላይ የጊዜ ቆይታው ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ድረስ የቆየ፡-

21. በምራዕብ አዲስ አበባ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በጉዞ ላይ ያለ (Deposit in Transit) ብር 149,307,069.73 የሚታይ ሲሆን በቅ/ጽ/ቤቱ ባንክ አካውንት (Book Balance) ላይ በአጠቃላይ ሌጀር ላይ ያልተመዘገበ ገቢ (Deposit not recorded in General Leger) ተብሎ የተያዘ ብር 273,087,594.71 እንዲሁም ክፍያ ተፈጽሞ በአጠቃላይ ሌጀር ላይ ያልተመዘገበ ወጪ (Payment not recorded in General Leger) ብር 84,177,034.51 መኖሩ፤

22. በምስራቅ አዲስ አበባ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ደግሞ በጉዞ ላይ ያለ (Deposit in transit) ብር 50,753,562.39 መኖሩ ታውቋል፡፡

23. ሁኔታው በባንክ ሂሳብ ማመዛዘኛ ላይ ያለውን የአሰራርና የክትትል ክፍተት ከማሳየቱም በተጨማሪ የተዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት ተዓማኒነት ያሳጣዋል፡፡

24. በመሆኑም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ሂሳቡ እንዲስተካከል፤ ለወደፊቱም በባንክ ሂሳብ ማመዛዘኛ አሰራር ላይ ያለው የአሰራርና የክትትል ክፍተት መስተካከል እንዳለበት ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. የገቢ ሂሳብ

4.1. በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ ህግ መሰረት ተሰልቶ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ የገቢ ሂሳብ፤

25. በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡት ደንብና

መመሪያዎች መሰረት መሰብሰብ ያለባቸው የገቢ ግብር፣ ታክስና ቀረጥ እና የመሳሰሉት መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር በሚገኙ 14 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **304,866,458.58** እንዲሁም በሌሎች 10 መ/ቤቶችና 1 ቅርንጫፍ ብር **5,016,649.10** በድምሩ ብር **309,883,107.48** ያልተሰበሰበ ግብር፣ የታክስና የቀረጥ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

26. በተጨማሪም የተያዘው ዋስትና ወደ ቀጥታ ገቢ ባለመቀየሩ ወይም ዋስትናው ባለመራዘሙ በ2 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **19,515,800**፣ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው ወጪዎች ባለመካተታቸው በ13 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር ብር 306,691,700.36፣ የግብይቱ ዋጋ ከጉምሩክ የግብይት ዋጋ ሲነፃፀር ልዩነት በመኖሩ በ4 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች **16,370,743.84** እንዲሁም ክፍያ በተፈፀመበት ቀን ባለው ምንዛሬ መሰረት ባለመሰላቱ በ4 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **3,677,947.00** በድምሩ ብር **346,256,191.20** ያልተሰበሰበ የቀረጥና ታክስ ሒሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

27. በመሆኑም ያልተሰበሰበው ግብር፣ ታክስ እና ቀረጥ ህጉን ተከትሎ መሰብሰብ እንዳለበት እንዲሁም ለወደፊቱም መሥሪያ ቤቶች የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን መሰረት ተከትለው መሰብሰብ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.2. <u>ያልተሰበሰበ የግብር፣ የታክስና የቀረጥ ሒሳብ</u>፤

28. በገቢዎች እና በጉምሩክ ኮሚሽን በተለያዩ አካላት በተደረገው ማጣራት የተገኘው ያልተሰበሰበ የመንግሥት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2016 በጀት ዓመት በ11 የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በጠቅላላው ብር **2,390,263,915.92**፣ በተለያየ ሂደት ላይ የሚገኝ የግብር ዕዳ በ10 የገቢዎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ብር **1,226,747,046.95**፣ በድምሩ ብር **3,617,010,962.87** ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

29. የግብር፣ የታክስና ቀረጥ ሂሳብ በወቅቱ ክትትል ተደርጎ ገቢ እንዲሆን ካልተደረገ የልማት ሥራዎች እንዳይፋጠኑ እንቅፋት ከመፍጠሩም በተጨማሪ በገቢ አሰባሰቡ ሂደት ላይ ያለውን የክትትል ክፍተት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ እና ዋናው መ/ቤት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ግብር ከፋዮች ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ቀጣይ እርምጃ በመውሰድ ያልተሰበሰበውን ቀሪ የቀረጥና ታክስ እዳ መሰብሰብ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.3. ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሳብ፤

30. መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት የሰጡበትን ሂሳብ በተገባው የውል ሥምምነት መሰረት በወቅቱ የሚሰበስቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በዱቤ ከሰጠው የማስታወቂያ አገልግሎት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሰበሰብ የቆየ ብር 168,480,898.30፣ የአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የህክምና አገልግሎት የሰጠበት ብር 75,601.27 በጠቅላላው ብር 168,566,499.57 በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

31. ገቢው በወቅቱ ክትትል ተደርጎ ካልተሰበሰበ ተቋማቱ በእቅድ የያዙትን ስራ እንዳያከናውኑ ጫና ከመፍጠሩም በተጨማሪ በገቢ አሰባሰቡ ሂደት ላይ ያለውን የክትትል ክፍተት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ያልተሰበሰበው ውዝፍ የገቢ ሂሳብ እንዲሰበሰብ ተገቢው ጥረትና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4. ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ፤

32. የተሰበሰበውን የገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን በናሙና ከታየው የገቢ ሂሳብ ውስጥ በጠቅላላው ብር 1,086,831.89 የመነሻ ሰነዱ ባለመቅረቡ የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም።

33. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙ እንዲሁም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.5. ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ፤

34. ህዳር 2007 ዓ.ም የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር የአሁኑ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣው የትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 6 አንቀጽ 6.2(12) ላይ የአገልግሎት ግዴታውን ሳያጠናቅቅ በራሱ ፍቃድ መሥሪያ ቤቱን ቢለቅ በትምህርት እና ሥልጠና ወቅት መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን ወጪ በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ከነወለዱ መክፈል እንዳለበት መመሪያው ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት

እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ለሥልጠና የላኳቸው ባለሙያዎች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ15 ዩኒቨርሲቲዎች 109 መምህራኖች የውል ግዴታቸው ሳይወጡ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ በመሆኑ በውሉ መሰረት ብር 40,108,135.41 እንዲከፍሉ ወይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

35. በውላቸው መሰረት ተመላሽ እንዲሆን ካላደረጉ ተቋማት ውስጥ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,156,785.61፣ መቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,244,857.00፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 5,535,244.00፣ ጂንካ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,152,864.00 እና ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,212,568.54 ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

36. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በውላቸው መሰረት መምህራኖቹ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢውን ጥረት እንዲያደርጉ፣ ይህ ካልሆነ ግን ገንዘቡን በውሉ መሰረት ማስመለስ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

4.6. በመንግሥት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፤

37. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4 አንቀጽ 21(1) ላይ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማጽደቅ እንዳለባቸው በተገለጸው መሰረት ኦዲት ተደራጊው መሥሪያ ቤቶች መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 37,304,100.19 የገቢ ተመን ሳይኖረው የተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመንግስት የተፈቀደ የማስከፈያ የዋጋ ተመን ሳይኖር ገቢ ከሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ብር 25,487,103.72፤ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች አገልግሎት ብር 7,592,819.86፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ብር 2,608,758.53፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

38. በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ እና መመሪያ መሰረት በጥናት እና በመረጃ የተደገፈ የዋጋ ማስከፈያ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል አቅርበው በማጸደቅ ገቢውን እንዲሰበስቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7. ገቢ ያልተደረገ የጉዳት ካሳ፤

39. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ወይም

አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ በንዑስ አንቀጽ 16.27.4 (ሀ እና ለ) መሰረት አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ የጉዳት ካሳ (መቀጫ) እንደሚከፍል እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% መብለጥ እንደሌለበት ተመልክቷል፡፡ መሥሪያ ቤቶች በዚሁ መሰረት መፈጸማቸው ሲጣራ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,126,360.86 የጉዳት ካሣ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ የጉዳት ካሳ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ብር 2,413,814.30፤ የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ብር 662,414.00 በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡

40. በውላቸው መሰረት ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ የዕቃ/አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ተቋማቱ የሚፈለገውን የጉዳት ካሳ ሰብስበው ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. ተሰብሳቢ ሂሳብ

5.1. በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

41. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 16(4) መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 2(4) መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች በዚሁ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ137 መሥሪያ ቤቶች እና በ20 የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች ቅ/ጽ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 32,934,537,850.57 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

42. የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 17,767,754,432.20፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 10,477,810,689.55፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 4,477,698,537.59 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 204,885,423.59 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 6,388,767.64 የቆይታው ጊዜው አይታወቅም፡፡

43. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሒሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የጤና ሚኒስቴር ብር 6,775,437,399.94፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 1,771,427,578.17፣ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,296,730,508.55፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 1,112,702,481.72፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,016,413,690.96፣ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ብር 972,319,143.50፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 697,156,838.06፣ የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 585,583,865.90፣ የፌዴራል ፓሊስ ኮሚሽን ብር 542,927,883.54፣ የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ብር 508,134,699.65 ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

44. በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ እንዲወራረድ ያለማድረግ ለመንግሥት ገንዘብ መባከን በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለባቸው፤ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሳቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ እንደማይችሉ የተረጋገጡት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ ለየተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.2. ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

45. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8(4መ) መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁንና በ22 መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 401,606,273.92 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡

46. የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው መሥሪያ ቤቶች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 253,373,189.31፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 92,213,567.20፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 13,127,830.72፣ የጤና ሚኒስቴር ብር 10,407,047.81፣ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ብር 8,537,077.51፣ የኢትዮጵያ ጤና መድን አገልግሎት ብር 8,490,691.60፣ የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ብር 6,648,957.51 ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

47. በተቋማቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሚታዩት ተሰብሳቢ ሂሳቦች የሂሳብ ምዝገባ መነሻ ሰነድ ሊኖራቸው ስለሚገባ፣ ሁኔታው ተጣርቶ ማስረጃቸው ሊቀርብ እንደሚገባ እና ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይከሰት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት

ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. የወጪ ሂሳብ

48. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውን፣ መጠቀማቸውን ተገቢውን ማስረጃ መቅረቡን እና ሂሳቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝቷል፡፡

6.1. ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ፤

49. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በደንብ ቁጥር 190/2002 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(2ለ) መሰረት ክፍያዎች ከመፈጸማቸውና ከመመዝገባቸው በፊት ስለወጪው ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር **762,606.47** ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

50. በመሆኑም ለክፍያው ማስረጃ እንዲቀርብ፣ ማስረጃው መቅረብ ካልቻለ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱ ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.2. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤

51. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በደንብ ቁጥር 190/2002 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(2ለ) መሰረት ክፍያዎች ከመፈጸማቸው እና ከመመዝገባቸው በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ28 መ/ቤቶች እና በ7 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በጠቅላላው ለተፈጸመው ክፍያ ብር **348,306,352.43** የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

52. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ከመዘገቡት መሥሪያ ቤቶች መካከል የጤና ሚኒስቴር ብር **197,461,069.92**፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር **43,783,700.00**፣ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር **21,103,004.28**፣ የቤተመንግሥት አስተዳደር ብር 19,567,997.53፣ የባህርዳር ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ብር **14,504,621.20**

ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

53. በመሆኑም ለክፍያዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ለክፍያዎቹ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ ለወደፊቱም ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3. በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤

54. የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን፤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ ሲፈጽም ክፍያ የሚፈፀመው የግንባታውን የክንውን ደረጃ መሠረት አድርጎ እና ከአማካሪ መሀንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር **38,570,539.43** መኖሩ ታውቋል፡፡ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር **28,765,923.00**፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር **5,789,602.07** ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

55. በመሆኑም በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች ማስረጃ እስኪቀርብላቸው ድረስ በተሰብሳቢ እንዲመዘገቡ፤ ለወደፊቱም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ ሥራው ከተሰራ እና ለወጪዉ የተሟላ ማስረጃ ከቀረበ በኋላ ሂሳቡ በወጪ መመዝገብ እንዳለበት ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.4. ደንብና መመሪያ ያልተከተለ የወጪ ሂሳብ፤

56. መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሙት ክፍያ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ተከትለው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ24 መ/ቤቶች፣ በ9 የገቢዎች እና በ3 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር **51,742,572.40** ደንብና መመሪያን ሳይከተል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

57. ደንብና መመሪያን ሳይከተል ክፍያ ከፈጸሙት መሥሪያ ቤቶች መካከል አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር **23,684,796.90**፣ ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር **9,278,149.59**፣ የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ብር **2,861,896.63**፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ብር **2,458,137.00** ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

58. መሥሪያ ቤቶች የሚፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አላአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6.5. በመስሪያ ቤቱ ለሌሉ እና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፤

59. የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ተራ ቁጥር 10 የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ አከፋፈል ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ/ወጪ ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች አንዱ በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ምክንያት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መውጣት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ በመመሪያው መሰረት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ደመወዝ ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ እንዳልተከፈላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ16 መ/ቤቶችና በ1 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በጠቅላላው ብር **408,462.57** በሥራ ላይ ለሌሉ እና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

60. ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ እና የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.6. በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቀድ የተፈጸመ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር፤

61. በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ዓ.ም አንቀጽ 31 መሰረት ጊዜያዊ ሰራተኛ መቅጠር የሚችለው የዘላቂነት ባሕርይ በሌለው የስራ መደብ ላይ ነው፡፡ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የስራ መደብ ላይ ጊዜያዊ ሰራተኛ መቅጠር የሚቻል መሆኑ የተመለከተ ቢሆንም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ሲሰኮ30/ጠ46/7/14 ባስተላለፈው ሰርኩላር በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ መስተቀር ከጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የሰራተኞች ቅጥር፣ ደረጃ እድገትና ዝውውር እንዳይፈጸም ባስተላለፈው ሰርኩላር መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ8 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት በጠቅላላው ብር **24,073,003.16** የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ሳያስፈቅዱ በቋሚ የሥራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን በኮንትራት በመቅጠር ክፍያ የፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

62. በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቀድ የኮንትራት ቅጥር ከፈጸሙት ተቋማት መካከል የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ብር 5,670,285.77፣ ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,297,842.99፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,128,560.34፣ የአለርት ኮምፕርሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 4,000,590.79፣ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

63. በመሆኑም ዘላቂነት ባለው የስራ መደብ ላይ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ ሰራተኞችን በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ ክፍያው ሊቆም እንደሚገባ፤ ለወደፊቱም የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር ለመፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማቅረብ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.7. <u>ዘላቂነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ የተፈጸመ የቀን ሰራተኞች ቅጥር</u>፤

64. በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ዓ.ም እና በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 5/2014 ዓ.ም መሰረት በቋሚ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ስራ ለመቅጠር ያልተፈቀደ ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ12 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቋሚ የሥራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን በቀን ሥራ በመቅጠር በጠቅላላው ብር 61,882,081.44 ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዘላቂነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ቅጥር ከፈፀሙ መ/ቤቶች መካከል ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,310,211.35፣ አምቦ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,938,834.79፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,888,374.50፣ ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,170,600.00፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,414,974.64 በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡

65. ዘላቂነት ባለው የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሥራ ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ ክፍያው ሊቆም እንደሚገባ ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.8. <u>ከሥራ ተቋራጮች ተመላሽ ያልተደረገ፣ ዋስትና ያልቀረበለት እና ያልታደሰ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ</u>፤

66. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ዋስትና መቅረቡን እና መታደሱን እንዲሁም ከተቋራጮች በሚቀርበው የግንባታ ሰርተፊኬት መሰረት የቅድሚያ ክፍያው በውሉ ላይ በተቀመጠው ፐርሰንት ልክ የጊዜ ገደቡን ጠብቆ ተመላሽ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 113,884,651.49፣ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,816,731.62፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,065,109.37፣ አጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ

ስልጠና ኮሌጅ ብር 10,956,410.69 በጠቅላላው ብር 171,722,903.17 ሥራው በመዘግየቱ እና በመቋረጡ ተመላሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ብር 180,784,765.14 ደግሞ በወሊጋ ዩኒቨርሲቲ የዋስትና ጊዜ ገደቡ ያለፈበት እና ያልታደሰ የቅድሚያ ክፍያ ሒሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

67. በሥራ ላይ የሚገኙ እና የቅድሚያ ክፍያ ቀሪ ገንዘብ ያለባቸው የሥራ ተቋራጮች በአስቸኳይ ዋስትናውን (ፐርፎርማንስ ጋራንቲ) እንዲያሳድሱ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የዋስትናው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት እንዲያሳድሱ የሚመለከተው ክፍል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.9. <u>በውሉ መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁ እና የተቋረጡ የግንባታ ፕሮጀክቶች</u>፤

68. በ11 ተቋማት የ131 ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሥራ ለማከናወን በብር 21,396,303,083.47 ውል የተፈጸመ ሲሆን ፕሮጀክቶቹ መጠናቀቅ ከሚገባቸው ጊዜ ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ድረስ የዘገዩ ሲሆን ሥራዎቹ የደረሱበት የግንባታ ደረጃ በፐርሰንት ከ1% እስከ 99% ድረስ ባለው ውስጥ የሚገኙ እና የፕሮጀክት ሥራው ሳይጠናቀቅ የተቋረጡ መኖራቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከፍተኛ መዘግየት ከታየባቸው ውስጥ የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 6 ፕሮጀክቶች ከ2 ወር እስከ 11 ዓመት፣ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ 37 ፕሮጀክቶች ከ2 ዓመት በላይ አስከ 10 ዓመት እና የመቐለ ዩኒቨርሲቲ 18 ፕሮጀክቶች ከ8 ወር እስከ 7 ዓመት ድረስ የዘገዩ ሲሆን ግንባታው ሳይጠናቀቅ የተቋረጠው ደግሞ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

69. በመሆኑም መጠናቀቅ ባለባቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ እና የተቋረጡ ግንባታዎች አፈጻጸም ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትሉ በመሆኑ ተቋማቱ ከሥራ ተቋራጮቹ እና ከአማካሪ ድርጅቶቹ ጋር በጋራ በመወያየት ለመዘግየታቸው ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ለይቶ መፍትሔ በመስጠት እና ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በመሥራት ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ የሚመለከታቸው የተቋማቱ አካላት ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ እንደሚገባ ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.10. <u>በመንግሥት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር የተፈጸመ ክፍያ</u>፤

70. መሥሪያ ቤቶች የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ሽልማቶችን እና የመሳሰሉትን ክፍያ ሲፈጽሙ በመንግሥት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና ተመን የወጣላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 18,566,635.65 የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

71. የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም የክፍያውን ተገቢነት ለማረጋገጥ

የማያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ለወደፊቱ ለክፍያዎቹ መመሪያና ተመን እንዲወጣላቸው መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.11. <u>በብልጫ፣ በድጋሚ እና ለለአግባብ የተፈጸሙ የተለያዩ ክፍያዎች</u>፤

72. ክፍያዎች በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 በዝርዝር የተገለጹት ሁኔታዎች ተሟልተው እና በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሰረት ክፍያዎች ከመፈጸማቸውና ከመመዝገባቸው በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለውሎ አበል ለደመወዝ እና ለተለያዩ ወጪዎች ክፍያ ሲፈጸም በ50 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር **41,159,044.07** በብልጫ፣ በድጋሚ እና ለለአግባብ የተፈጸሙ የተለያዩ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲቱ ታውቋል፡፡ በብልጫ፣ በድጋሚ እና ለለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙት ውስጥ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር **9,134,746.90** ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር **4,628,702.20**፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ብር **4,090,302.94**፣ የኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኮሚሽን ብር **3,620,000.00**፣ የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል ብር **3,504,479.06** የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ብር **2,316,339.92** እና ጂማ ዩኒቨርስቲ ብር **2,315,703.07** ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

73. በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ሥርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትለው ክፍያዎች መፈጸም እንደሚገባቸው፣ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.12. <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ</u>፤

74. የፌዴራል መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል መስከረም 25 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ገ/ሂ/1/53/86 ባስተላለፈው ሰርኩላር መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን እና ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ70 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **404,728,718.36** የመንግሥትን የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

75. ከዚህ ዉስጥ በጨረታ መገዛት ሲገባው ያለጨረታ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር

229,481,435.31፣ መስፈርቱን ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ ብር 16,558,513.19፣ ጨረታ ሳይወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 107,047,626.85፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 5,964,995.41፣ በኤሌክትሮኒክስ (EGP) ያልተፈጸመ ግዥ ብር 29,059,664.23፣ መስፈርቱን ሳያሟላ በለቀማ የተፈጸመ ግዥ ብር 16,616,483.37 ናቸው፡፡

76. ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ብር 40,816,348.69፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 17,554,986.93፣ የብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን ብር 17,206,309.53፣ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,631,856,71፣ በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር-2 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ብር 15,093,062.31 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

77. በመሆኑም ተቋማቱ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም እንዳለባቸው፤ ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ውጭ ግዥ መፈፀም ሲያስፈልግ ተቋማት ጥያቄያቸውን ለሚመለከተው አካል አቅርበው ሲፈቀድ ብቻ ግዥውን መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በለቀማ የሚፈጽሙት ግዥዎች ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለግና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለመሥሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደሚያስገኝ በቅድሚያ በተጨባጭ ማስረጃ መረጋገጥ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም የተጠቀሱት የአሰራር ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.13. <u>የተፈጸሙ ግዥዎች በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆናቸው ወይም አገልግሎቱ ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈጸሙ ክፍያዎች፤</u>

78. የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 መሰረት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር (Specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱን እና አስፈላጊ ሲሆን እቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ13 መ/ቤቶች በጠቅላላው በብር 70,917,003.38 የተፈጸሙ ግዥዎች በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆናቸው ወይም አገልግሎቱ ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ክፍያዎች የተፈፀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ክፍያዎች ከፈፀሙ ተቋማት ውስጥ የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል ብር 30,302,136.53፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

ብር 2,823,323.30፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 2,363,775.78 እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ብር 2,226,604.50 በዋንኛነት ይጠቀሳል፡፡

79. ግዥዎች በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት ለመፈጸማቸው በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ክፍያ የሚፈጸም ከሆነ ላልተፈለገ አሰራር መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በተጨማሪ የንብረቶቹን ወይም የተሰጠው አገልግሎት ጥራትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡

80. በመሆኑም ተቋማቱ የፈጸሟቸው የንብረት/ የአገልግሎት ግዥዎች በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆናቸው ወይም አገልግሎቱ ለመሰጠቱ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በቅድሚያ በቴክኒክ ኮሚቴ እንዲረጋገጥ ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.14. <u>ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>፤

81. የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9(3) መሰረት ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃው ወደ መሥሪያ ቤቱ ዕቃ መጋዝን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበት በተመለከተው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ8 መ/ቤቶች በጠቅላላው በብር 6,592,841.59 የተገዙት ንብረቶች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

82. የተገዙትን ንብረቶች ገቢ ካላደረጉት ተቋማት ውስጥ የህዝብ እንባ ጠባቂ ብር 1,870,811.95፣ የቤተ መንግሥት አስተዳደር ብር 1,829,160.70 እና መቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,509,707.81 በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

83. በመመሪያው መሰረት ተገዝተው ወደ ንብረት ክፍል መግባት የሚገባቸው ንብረቶች ገቢ ካልተደረጉ ግዥው ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ሁኔታን ከመፍጠሩም በተጨማሪ የመንግሥት የሀብት አያያዝና አጠባበቅ ሥርዓቱን ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል፡፡

84. በመሆኑም ገቢ ያልተደረጉት ንብረቶች ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ መደረግ የሚገባቸው ንብረቶች ገቢ ሳይደረጉ ሂሳቦቹ እንዳይወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.15. <u>በአማካሪ መሐንዲስ የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ</u>፤

85. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ

28(5ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ክፍያ የሚፈፀመው የሥራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ ምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት በጠቅላላው በብር 38,439,223.24 ውል ከተገባው ውስጥ ብር 7,912,141.67 ክፍያ ሲፈጸም የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ እና በአማካሪ መሐንዲስ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

86. የክፍያው ተገቢነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው በመሆኑ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ክፍተት እንዳይከሰት ኢንስቲትዩቱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.16. ለ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ማስፈፀሚያ ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ክፍያ፤

87. የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሰጥ መንግሥት በወሰነው መሰረት የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ነሐሴ 2014 ዓ.ም የፈተና አሰጣጥና አፈጻጸም ማኑዋል ያወጣ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲዎቹ ለፈተናው አፈጻጸም የሚሆን በጀት መድቧል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች በተመደበላቸው በጀት መሰረት ክፍያ የሚፈጽሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,912,645.49፣ የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,461,054.00፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 211,136.48፣ በጠቅላላው ብር 15,584,835.97 ለፈታኞች የአልጋ እና የምግብ አገልግሎቶች ከዩኒቨርሲቲዎቹ መደበኛ በጀት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

88. በመሆኑም ለ12ኛ ክፍል ፈተና የተያዘው በጀት የማይበቃ ከሆነ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ተጨማሪ በጀት ማስፈቀድ እንጂ ለመደበኛ ሥራ አገልግሎት ከተመደበው በጀት ላይ ክፍያ መፈጸም ተገቢነት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱ አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት ለተቋማቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. ተከፋይ ሂሳብ

13.1. በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፤

89. በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ90 መ/ቤቶች እና በ8 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,385,452,268.08 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት

ብር 4,061,941,771.22፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 1,868,141,165.30፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 348,509,106.45 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 4,762,782,529.31 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 344,077,695.80 የቆይታው ጊዜው የማይታወቅ ነው፡፡

90. ውዝፍ ተከፋይ ሒሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 525,173,134.02፣ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ብር 129,599,303.59፣ የመቀሌ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ብር 108,922,703.68፣ የመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ብር 90,682,944.21፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

91. ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ አለመክፈል የተከፋይ ሂሳብ ክምችትን ሊጨምር ከማስቻሉም በላይ ተቋማቱን ለተጨማሪ ቅጣትና ወለድ ይዳርጋል፡፡

92. በመሆኑም የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች ትክክለኛ ዕዳዎች መሆናቸውን በማረጋገጥ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል እንዲከፈል፤ መከፈል የማይችል ከሆነ ደግሞ ተገቢ የሆነ ማጣራት በማድረግ አሰፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

13.2. <u>ለተከፋይ ሂሳቡ ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ</u>፤

93. በፌደራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ(5ሀ) መሰረት ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ሥልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለባቸው በተመለከተው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 42,770,439.04 ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

94. ተከፋይ ሒሳቡ ለማን እንደሚከፈል ዝርዝር ማስረጃ ካላቀረቡት ተቋማት ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የማዕድን ሚኒስቴር ብር 12,622,547.20፣ የጤና ሚኒስቴር ብር 8,266,131.86፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 7,706,904.98፣ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 4,216,649.29 እና የግብርና ሚኒስቴር ብር 3,662,443.02 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

95. በመሆኑም ሂሳቡ በተከፋይ ለምን እንደተያዘ ሁኔታው ተጣርቶ ለሂሳቡ ተቀጽላ ሌጀር እንዲዘጋጅለት እንዲደረግ፤ ሂሳቡም እንዲከፈል ተገቢ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

14. የበጀት አጠቃቀም

96. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሰራበት በጀት የተገኘ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

14.1.ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ፤

97. በፌደራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን የመደበኛ፣ የካፒታል እና የውስጥ ገቢ የወጪ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተቋማት የበጀት አጠቃቀማቸውን በመመሪያው መሰረት እያከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2016 በጀት ዓመት በየፕሮግራሙ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር በማነጻጸር ኦዲት ሲደረግ ከመደበኛ በጀት በ19 መ/ቤቶች ብር **1,103,727,917.05**፣ በ4 መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢ ብር **108,978,757.18** እና በ9 መ/ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር **416,126,365.43** በጠቅላላው ብር **1,628,833,039.66** ለሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ተጠቅመው ተገኝቷል፡፡

98. ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀቱ በላይ ሥራ ላይ ካዋሉት መ/ቤቶች መካከል የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር **421,886,276.91**፣ የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር **213,945,934.55**፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር **209,796,389.46**፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር **197,927,673.97**፣ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር **102,224,580.50** እና የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር **100,283,129.73** ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

99. በበጀት ህጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይፈፀም ለሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ከማስከተሉም በተጨማሪ የዕቅድ ዝግጅቱ በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ተቋማቱ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትለው የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

14.2. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

100. በፌደራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን የመደበኛ፣ የካፒታል እና የውስጥ ገቢ የወጪ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር

እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተቋማት የበጀት አጠቃቀማቸውን በመመሪያው መሰረት እያከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2016 በጀት ዓመት በየፕሮግራሙ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ በ115 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 3,094,529,723.08፣ በ20 መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢ ብር 284,457,520.07 እና በ55 መ/ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር 11,114,730,854.13 በጠቅላላው ብር 14,493,718,097.28 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ተገኝቷል።

101. የተደለደለላቸውን በጀት ሥራ ላይ ካላዋሉት መ/ቤቶች መካከል የግብርና ሚኒስቴር ብር 7,815,411,448.84፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ብር 573,609,032.20፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 486,798,917.19፣ የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 420,353,135.47፣ የአርቲፊሻል ኢተለጀንስ ኢንስቲትዩት ብር 350,472,242.29፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ብር 339,117,140.83፣ የጅግጅጋ የኒቨርሲቲ ብር 306,477,827.43፣ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 300,145,735.34፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 245,209,968.16፣ የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ ብር 216,456,077.26፣ የጤና ሚኒስቴር ብር 211,137,282.81 እና የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 210,074,955.61 በዋንኛነት ይጠቀሳሉ።

102. የተፈቀደውን የወጪ ሂሣብ በጀት በዕቅዱ መሠረት ያለመፈጸሙ የተቋማቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ ከማድረጉም በተጨማሪ የዕቅድ ዝግጅቱ በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በኃላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ እና በተጨማሪም በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግ ሥራ ላይ ሊውል የማይችለውን በጀት ሌሎች የበጀት እጥረት ያለባቸው መሥሪያ ቤቶች ይጠቀሙበት ዘንድ ለይተው በማውጣት ለገንዘብ ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

15. <u>ንብረት</u>

15.1.<u>በቋሚና አላቂ ንብረቶች ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

103. የተቋማት የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

ተራ ቁጥር	የግኝቶቹ ዝርዝር	የመሥሪያ ቤቶች ብዛት	የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብዛት
1.	ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ ያልሰጡ፤	**10**	
2.	ለየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ፤	**2**	
3.	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ፤	**7**	
4.	የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያላደረጉ፤	**9**	
5.	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም በቆጠራው ውስጥ ያልተካተቱ ንብረቶች፤	**1**	
6.	ለአላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ፤	**7**	**4**
7.	ያለአገልግሎትየተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው፤	**48**	**5**
8.	አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው፤	**80**	**14**
9.	ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ሥራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚሰራባቸው፤	**13**	**2**
10.	ከተቋማቱ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ፤	**24**	**1**
11.	በተቋማቱ በሥራ ላይ ያሉ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ እና የጠፉ ንብረቶች እንዲተኩ ያላደረጉ፤	**1**	**2**
12.	የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ያላረጋገጡ፤	**1**	
13.	የመጠቀሚያ ጊዜያቸውው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን ያላስወገዱ፤	**16**	**2**
14.	የተተው፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ የሚገኙ ንብረቶች የተገኘባቸው፤		**10**
15.	የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው፤	**2**	**1**
16.	የንብረት ምዝገባ በኢፍሚስ ሲስተም እንዲመዘገብ ያላደረጉ፤	**2**	
17.	በጸጥታ ምክንያት የተዘረፉ ንብረቶች የተገኘባቸው፤		**1**
18.	ንብረቶቹ ርክክብ ሳይደረግ የተገኙባቸው፤	**1**	

104. በንብረት አስተዳደሩ ላይ የታዩት የአሰራር ክፍተቶች ንብረቶቹን ለብክነት የሚያጋልጡ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

15.2.<u>በተሽከርካሪዎች ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

105. የተቋማት የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

ተራ ቁጥር	የግኝቶቹ ዝርዝር	ግኝቱ የተገኘባቸው ተቋማት ብዛት		የግኝቶቹ አይነትና ብዛት			ሌሎች መግለጫ
		መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ ቤቶች	መኪኖች	ሞተር ብስክሌቶች	* ሌሎች	
1.	ሊብሬ (የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር) ያልቀረበላቸው፤	26	2	136	54	29	28 ትራክተር 1 ዶዘር
2.	ያለ አገልግሎት/ በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው፤	58	10	575	52	20	15 ትራክተር 3 ጀነሬተር 1 ዶዘር 1 ግሬደር
3.	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፤	7	2	3	41	30	25 ትራክተር 5 ፎርክሊፍት
4.	የሞተር ቁጥር የሌላቸው፤	1	1				
5.	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶች እናድርጅቶች ሥም የሆነ፤	40	2	415	2		
6.	በባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እና በመኪናው አካል ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል የታዩ ልዩነት፤	1		3			
7.	በባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እና በመኪናው አካል ላይ በተመለከተው የሞተር ቁጥር መካከል የታዩ ልዩነት፤	1	1	2			

ተራ ቁጥር	የግኝቶቹ ዝርዝር	ግኝቱ የተገኘባቸው ተቋማት ብዛት		የግኝቶቹ አይነትና ብዛት			ሌሎች መግለጫ
		መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች	መኪኖች	ሞተር ብስክሌቶች	* ሌሎች	
8.	ለተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ መዝገብ ያላዘጋጁ፤	3	2	81			
9.	የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የማይሰራ፤	5	1	39	4		
10.	ሊብሬያቸው ቀርቦተሽከርካሪዎቹ በአካል ያልተገኙ፤	1		5			
11.	አገልግሎት የማይሰጡ(መወገድ) ያለባቸው ተሽከርካሪዎች፤	10	1	107	5		
12.	ለአሮጌ ተመላሽ እቃዎች ገቢና ወጪ ማድረጊያ ያላዘጋጁ፤	2		2			
13.	የጠፉ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው፤	4		39	5		
14.	በቱሪስት ስም ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉ ተሽከርካሪዎች ከአገር ስለመውጣታቸው ወይም አገር ውስጥ ስለመቅረታቸው ያልታወቀ፤		1	4			

ሌሎች በሚለው ዓምድ ሥር የተመለከቱት ትራክተር፣ ዶዘር፣ ግሬደር፣ ፎርክሊፍት፣ ጀነሬተር እና የመሳሰሉትን ይይዛል፡፡

106. በተቋማቱ የተሽከርካሪዎች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ እና ሌሎች በአሰራር ላይ የታዩት ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት መስተካከል እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

16. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር ፕሮጄክት ኦዲት፤

107. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ ኦዲት ሲሆን፣ የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

108. በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ 368 የተከታታይ፣ 4 የማረጋገጫ ኦዲቶች፣ 1 የተጠቃለለ የገንዘብ ሚኒስቴር ማጠቃለያ እና 13 የግብዓት ኦዲት (ለተጠቃለለ የገንዘብ ሚኒስቴር ኦዲት ግብዓትነት) እና 6 ልዩ ኦዲቶች በድምሩ 392 ኦዲቶችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም ሲታይ 361 የተከታታይ ኦዲት፣ 1 የተጠቃለለ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለተጠቃለለው የገ/ሚ/ር ሪፖርት መነሻ የሚሆኑ በ28 የክልል ፋይናንስ ቢሮች፣ ክልል ሴክተር ቢሮዎች፣ ወረዳ እና ከተማ አሰተዳደር ጽ/ቤቶች የተከናወነ ኦዲት እና 4 ልዩ ኦዲቶችን ድምር 394 (100.51%) ኦዲቶችን ማከናወን ተችሏል፡፡

17. የመንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ፤

109. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላከው የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት በመስጠት የገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ መቅረብ እንዳለበት ይጠቅሳል፡፡ በዚሁ መሰረትም ሪፖርቱ ተሰርቶ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

18. <u>የፌደራል መንግስት ለክልሎች የሰጠውን ድጋፍ እና ድጎማ በጀት የኦዲት ሪፖርት በተመለከተ፤</u>

110. የፌዴራል መንግሥቱ ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት የማድረግ ሥልጣን በህገመንግስቱ አንቀጽ 94/2 እና በአዋጅ ቁጥር 982/2008 እንደተሻሻለው 1146/2011 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 16 ለፌዴራል ዋና ኦዲተር የተሰጠ እና ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችም በክልሎቻቸው ተመሳሳይ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው በመሆኑ ይህን የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የነጠላ ኦዲት አዋጅ ቁጥር 1251/2013 እንዲወጣ ተደርጓል።

111. በዚሁ መሰረት የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በኦሮሚያ ክልል 307፣ በአማራ ክልል 155፣ ሲዳማ ክልል 103፣ ሶማሌ ክልል 20፣ ሐረሪ ክልል 16፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 18፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል 11፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል 54፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል 16፣ የትግራይ ክልል 128፣ የጋምቤላ ክልል 22፣ የአፋር ክልል 14፣ የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር 16 መ/ቤቶች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 16 ፕሮጀክቶች በበጀት መጠን በአጠቃላይ ብር **235,555,785,842.49** በነጠላ ኦዲት ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በኦዲት ግኝቶች ላይ

የታዩትን ክፍተቶች በተሰጠው አስተያየት መሰረት አሰፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ፤

112. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶች፤ እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት ወጪ ቆጣቢና ዉጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ ማዋላቸውን፣ የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መፈጸማቸውን ፣የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ግቦችን ሊያሳካ በሚችል መልኩ መከናወናቸውን እና የሴቶችን፤ የህፃንትን ተጠቃሚነት ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ በመጨመር በየካቲት 2016 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2017 የሚጠናቀቁ 32 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችና እና 8 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በድምሩ 40 ኦዲቶችን በእቅድ ተይዘው ነበር፡፡

113. በዚህም መሠረት 31 አዲስ ክዋኔ ኦዲቶች እና 8 የክትትል ኦዲቶች በድምሩ የ39 ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተጠናቅዋል፡፡ የእቀድ አፈጻጸሙም 97.5% ሲሆን ሪፖርቹም ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልከዋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ በተከበረው ም/ቤት የተጠየቁ ሁለትና ሰባቱ የአካባቢ ኦዲት ላይ ያተኩሩ ሲሆን፤ በኦዲቱ የታዩና የምክር ቤቱ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. **<u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የጊዶሌ፣ የመጆ እና የዶንጓራ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ፤(በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በተጠየቀው መሰረት የተሰራ)</u>**

114. በጊዶሌ፣ በመጆ እና ዶንጓራ ውሃ መጠጥ ፕሮጀክቶች የግንባታ ቅድመ አዋጭነት /Pre-Feasibility study/ እና ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት ፕሮጀክት መሰረታዊ ይዘቶች ማለትም የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ አዋጭነትና የቴክኒክ አግባብነት እና አካባቢያዊ

ተፅዕኖ ባካተተ መልኩ ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ አዋጭነት እንዲሁም መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ የአዋጭነት ጥናትና የዝርዝር ዲዛይን ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤

115. የጊዶሌ ውሃ መጠጥ ፕሮጀክት የቧንቧ አቅርቦትና መገጣጠሚያ እቃዎች ወደብ ላይ በ15 ቀናት ዉስጥ ባለማንሳቱ ተጨማሪ 257 ቀናት በመቆየቱ ለኮንቴይነር ኪራይ (Demurrage) እና ለመጋዝን ኪራይ (Storage Demurrage) በድምሩ ብር 11,491,411.25 (አስራ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አንድ ሺ አራት መቶ አስራ አንድ 25/100 ብር) ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

116. የጊዶሌ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የዲዛይን መሻሻል ተከትሎ በግንባታ ልዩነት (Variation) በመፈጠሩ ፕሮጀክቱ 72% የደረሰ ሲሆን ከተያዘለት በጀት በላይ ጠቅላላ ብር 25,679,837.52 (ሃያ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ከ52/100) እንዲሁም $ 250,935.81 (ሁለት መቶ አምሳ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አምስት ከ81/100 ዶላር) ተጨማሪ ወጪ መሆኑ፤

117. የጊዶሌ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የውሃ ማከማቻ (Reserviors) በመጀመሪያ ዲዛይን የተቀመጡ ቦታዎች በመሬት መንሸራተትና በተደራሽነት (Accessibility) ጋር በተያያዘ የውሃ ማከማቻው መገንቢያ ቦታ በትክክል ያልተጠና እና ከውሀው መገኛ ጉድጓድ (Borehole) ወደ ማቀባበያ ጣቢያዎች ወደ ማከፋፈያ የውሃ ማከማቻ (Reserviors) የሚመጣው የዋና የግፊት መስመር (Pressure Main) ለመዘርጋት የታቀደው መስመር በአካባቢው በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የመሬት ናዳ ያላገናዘበ መሆኑ፤

118. የመጀ እና ዶንጎራ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የግንባታ ቅድመ አዋጭነት /Pre-Feasibility Study/ እና የፕሮጀክት ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት ባካተተ መልኩ የቅየሳ ስራ፣ የአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ፣ የመስክ ዲዛይኖች መለኪያዎች፣ የከርሰ ምድር አፈር ፍተሻ/ምርመራ ሲካሄድ ከፕሮጀክቱ ተዛማጅነት ባላቸው መስፈርት መሰረት ወካይ የከርሰ ምድር (አፈር ናሙና) በመውሰድ ፍተሻ /ምርመራ በማድረግ የተቀመጠውም የአፈር ምርመራ ዘዴ እና ተደራሽነት ያካተተ ዝርዝር የአዋጭነት ጥናትና ዲዛይን በበቂ ጥናት ያልተደገፈ በመሆኑ የመጀ የውሃ መገኛ ጉድጓድ የመከነ ሲሆን የዶንጎራ የመጀመሪያው የውሃ ድፍርስ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ጤና ድርጅትና በኢትዮጵያ ውሃ ቁጥጥርና ጥራት መዳቢ ባለስልጣን ከተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለመጠጥ አገልግሎት እንዳይውል የታሸገ ሲሆን፣ለዚህም የወጣው ወጪ ብር 16,906,422.98 መሆኑ፤

119. የመጀ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ብር 56,360,889.79 ወጪ የተደረገበት ሲሆን እ.አ.አ October, 2016 አዋጭነት ጥናት የተጠና ቢሆንም በአዋጭነት ጥናት ወቅት በጥናቱ መታየት ያለባቸዉ ባለመታየታቸው ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር ሲገባ የውሃ መገኛ ጉድጓድ ፍተሻ (Flesh) ሳይደረግ፣ የግንባታ ስራ እና የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራዎች ገጠማ ሥራዎች ተገጥሞ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ግን ፍተሻ ሲደረግ የውሃ ጉድጓዱ የመከነ መሆኑ፤

120. የፕሮጀክቱ ወጪ የሚሸፈነው በጋራ መዋጮ ሲሆን በዚሁ መሰረትም በተቀመጠው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ተግባራዊ ያልተደረገ እና አፈፃፀሙ ላይ ክፍተት ያለበት ሲሆን ለማሳያም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሚጠበቀው መዋጮ መጋራት ድርሻ /Matching Fund/ ብር 34,810,324.28 የሚጠበቅ ሲሆን ብር 14,994,058.00 ወደ ክልል ፋይናንስ ቢሮ ዋሽ ፕሮግራም ፌዝ-2 አካውንት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ከሲዳማ ክልላዊ መንግስት የሚጠበቀው መዋጮ መጋራት ድርሻ /Matching Fund/ ብር 54,436,071.37 የሚጠበቅ ሲሆን ብር 25,436,071.37 ወደ ክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ዋሽ ፕሮግራም ፌዝ-2 ገቢ ያላደረጉ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2. <u>በኢትዮጵያ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አፈጻጸም፤</u>

121. የመንግሥት ፕሮጀክት አስተዳደር እና የአመራር ሥርዓት አዋጅ 1210/2012 ከወጣ በኋላ በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ወደ ቅድመ አዋጭነት፣ ወይም አዋጭነት ጥናት፣ ቅደም ተከተል ማስያዝና ወደ መረጣ ዑደት ሊተላለፍ የሚችለው በፕላንና ልማት ሚኒስቴር በፕሮጀክቶች ገለልተኛ አዋጭነት ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ፣ አዋጁ አስቀምጧል። በዚሁ መሰረትም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና በታዩ የመንግስት ፕሮጀክቶች አስፈጻሚ ተቋማት የተከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሳይሰራላቸው በጀት ተፈቅዶላቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤ ለአብነትም፡-

122. 52 የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ እና 42 የመስኖ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ግምገማ ሳይደረግላቸው ፣ በጀት ተፈቅዶላቸው ወደ ትግበራ የገቡ መሆኑ፤

123. በተጨማሪም የፋይናንሻል እና የፊዚካል እቅድ መርሃ-ግብር ሳይዘጋጅላቸው በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች በተገኘ መረጃ መሠረት 2013-2016 ዓ.ም. የተጀመሩ ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ 8 የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ 15 የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ 12 የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 10 የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ በድምሩ 45 ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤ ከዚህ በተጨማሪም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ፕሮጀክቶች ያሉበት ሁኔታ በጋራ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በፐላን ሚኒስቴር ተገምግሞ እና የፋይናንሻልና የፊዚካል አፈጻጸማቸው ሳይገመገም ባሉበት ሁኔታ በመቀጠላቸው፡-

124. በናሙና ከታዩ 4 ዩኒቨርስቲዎች የሚያስገነቡዋቸው ግንባታዎች እና 147 የመስኖ ፕሮጀክቶች ከአንድ አመት እስከ 7 አመት የዘገዩ መሆናቸው፤

125. በናሙና ከታዩ 296 የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ አራት አመትና ከዚያ በላይ የዘገዩ እና ከዚህ ውስጥ 127 ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ ያልተገኘላቸው መሆኑ፤

126. ከ267 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት የጠየቁ 20 የሚሆኑ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክቶች መኖራቸው እና ዘጠኙ ፕሮጀክቶች ከ 100% እስከ 200% ተጨማሪ በጀት ያስከተሉ መሆኑ፤

127. መጀመሪያ ከተመደበላቸው በጀት ከ78% እስከ 760% ተጨማሪ ተደርጎ ብር **17,254,150,104.00** ተጨማሪ ገንዘብ የጠየቁ የመስኖና በዩኒቨርሲቲዎች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

128. በእቅድ ከተያዘ በጀት ብር 13.2 ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ በጀት የወጣባቸው ከ180 በላይ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ መኖራቸው ከዚህ ውስጥ ከ75% በላይ ተጨማሪ ወጪ የወጣላቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

129. በናሙና በታዩት በሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክቶቹ የተጠናቀቁ እና ስራ የጀመሩ ቢሆንም ፕሮጀክቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ብር **2,964,476,085.00** በጀት ተመድቦ የተለቀቀላቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

130. በአምስት ዩኒቨርሲቲዎች ብር **1,110,208,910.22** በጀት የተለቀቀላቸው ቢሆንም ገንዘቡ ግን ለፕሮጀክቶቹ ሥራ ያለዋለ መሆኑ፤

131. ፕሮጀክት ከጽንሰ ሀሳብ ጀምሮ እስከ ትግበራ ድረስ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ የሚያዝበት፣ የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትና የመረጃ

ቋት (Database) በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አለመኖሩ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

3. በባዮ እና ኢ-መርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የባዮ ቴክኖሎጂ የምርምር አፈፃፀም በተመለከተ፤

132. የዘመናዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምርና ልማትን ማስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም፣ ይህን ዘርፉ የሚያግዝ ፖሊሲ በ2011 ዓ.ም በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ጸድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

133. ኢንዱስትሪው ከተመሰረተ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም እስካሁን የግብርና ማሽነሪ ምርቶችን የሚያዘምኑና የሚያሻሽሉ የምርምርና ጥናት ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም በዘርፉ ከተሰማሩ ኩባንያዎች ጋር በቅንጅት በመስራት የዘርፉን የቴክኖሎጂ አቅም ለማሳደግ ወይም ለማሻሻል ያልሰራ መሆኑ፤

134. ኢንስቲትዩቱ በባዮ ቴክኖሎጂ ምርምር ወደ ምርትነት እንዲሻገሩ የሚፈለጉ ቁልፍ የባዮቴክኖሎጂ ውጤቶችን አስቀድሞ በጥናት በመለየት እና ምርምር በማድረግ ለምርምር ማእከላት የሚያሳውቅበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

135. ኢንስቲትዩቱ በይርጋለም ግብርና ጽህፈት ቤት በኩል ሁለት የምርምር ውጤቶችን የማስተዋወቅ ስራ የሰራ ቢሆንም፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የባዮ ቴክኖሎጂ ምርቶች ከቤተ ሙከራ ወደ ገበያ በማውጣት ለተጠቃሚው ለድህነት ቅነሳ፣ ለምግብ ዋስትና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለጤና አጠባበቅ እና ለአካባቢ ጥበቃ እንዲውሉ የባዮ ቴክኖሎጂ ምርምር በማድረግ ችግር ፈቺ ሥራዎች ያልተሰራ መሆኑ፤

136. ኢንስቲትዩቱ ከአዳሚ ቱሉ ግብርና ምርምር ማዕከል ጋር አልጌ ለመድሃኒት እና ለምግብነት እንዲውል የሚሰራ ቢሆንም፣ ምርቱን ከማስፋፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ከማድረግ አንፃር ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን አለማድረጉ፣ ቴክኖሎጂን ከማሸጋገር ጋር ተያይዞ የተካሄዱ ምርምሮች ወደ ማህበረሰቡ የማሸጋገር ተግባር ያልተከናወነ መሆኑ፤ ከዚህ ቀደም ተሰርተው ሪፖርት የተደረገባቸው ምርምሮች እስከአሁን ድረስ ወደ ማሸጋገር ተግባር ያልተገባ መሆኑ እንዲሁም በ2014 ዓ.ም በአመታዊ እቅድ ለ252 ሰዎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ ለ155 ሰዎች (61%) ብቻ የተሰራ መሆኑ፤

137. በኢንስቲትዩቱ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጋራ በሚሰሩ ሶስት የምርምር ፕሮጀክቶች ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ወደስራ እንዲገቡ የተደረገ ቢሆንም በጠቅላላው ብር **3,581,578.00** ወጥቶባቸው የተቋረጡ መሆኑ፤

138. በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በአቮካዶ ዘይት ዙሪያ ዝርያዎችን በመለየት የምርምር ስራ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን፤ በእንስሳት ዙሪያ ምርምር ለማካሄድ ጥናት የተደረገ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ተገቢውን ድጋፍ ባለማድረጉ የምርምር ስራው በወቅቱ ተጠናቆ ችግር ፈቺ እንዳይሆን ተፅእኖ የፈጠረ መሆኑ፤

139. በኢንስቲትዩቱ መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 388/2008 መሰረት በሕግ የተለዩ የባዮቴክኖሎጂ ውጤቶችን ኢንስቲትዩቱ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት ቁጥጥር እንዲደረግባቸው አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ፍቃድ መስጠት፣ መቆጣጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እገዳ ማድረግ የሚገባው ቢሆንም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ፍቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እገዳ የመጣል ስራ እየሰራ አለመሆኑ፣ በኦዲቱ ታይቷል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

4. <u>በአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር ስራዎች እና ፈንድ አጠቃቀም በተመለከተ፤</u>

140. በሀገር አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የምርምር አካባቢዎች ወይም ሀገራዊ የጤና ምርምር አጀንዳዎች በጤና ሚኒስቴር ያልተለዩ በመሆኑ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ምርምር ሥራዎች ተመራማሪዎች በሚያቀርቡት የምርምር አካባቢ (ፕሮፖዛል) ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የታሰበውን ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ፤

141. በ2016 በጀት ዓመት ቀላልና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ መመርመሪያ ዘዴዎች በኤች. አይቪ. ኤድስ፤ ጉበት ላይ ቲቢ እና የመሳሰሉት ላይ ምርምር የተደረገ ቢሆንም በስፋት አምርቶ በጤና ተቋማት ጥቅም ላይ ማዋል ያልተቻለ መሆኑ፤

142. በ2017 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት ለሴል ማሳደጊያ የሚሆን የጥጆች ሴረም (ሴሎች ለማሳደግ የሚረዳ ከጥጆች የሚወሰድ ደም) እና ራቢት ፕላዝማ ለማምረት 25% ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፤

143. በኢንስቲትዩቱ 2015 በጀት ዓመት 150 የባህላዊ መድኃኒት የሚውሉ የዕፅዋቶች አይነት የመጠበቅ ሥራ የተጀመረ ቢሆንም፤ ዕፅዋቶቹ ለመድኃኒትነት ስለመዋላቸው የተረጋጋጠበት ማስረጃ ያልቀረበ እና የባህል ሕክምና አዋቂዎች በአገልግሎት ላይ የሚያውሏቸው መድኃኒቶች የደህንነት፤ የፍቱንነት እና የመድኃኒቶች አዘገጃጀት የአጠቃቀም መጠን መረጃ በሳይንሳዊ ጥናት (ምርምር) ላይ የተመረኮዘ አለመሆኑ፤

144. ኢንስቲትዩቱ ከ10 በላይ ከባህላዊ ህክምና አዋቂዎች ባለሙያዎች ጋር ውል የገባ ቢሆንም በ2017 ዓ.ም ሁለተኛ ሩብ ዓመት ከአንድ ባለሙያ ጋር ብቻ የደህንነት (acute/sub-acute toxicity) ጥናት (ምርምራ) ሥራ የተጀመረ መሆኑ፤

145. በ2015 በጀት ዓመት የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ችግሮች ለመፈታት ብር 14,750,000.00 ወጪ በማድረግ፤ ከሽታ እና ከጭስ ነፃ የሆነው የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ (Bio-medical waste-incinerator) ከተገዛ ሁለት ዓመት ያስቆጠረ እና በ2023 የኢንጂነሪንግ ባለሙያ በአምራች ካምፓኒ የኢንስኔሬተር አጠቃቀሙን በተመለከተ ሥልጠና እንዲያገኝ የተደረገ ቢሆንም፤ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ፤

146. በኢንስቲትዩቱ የምርምር ጥናት ሂደታቸውን ያጠናቀቁ ምርቶች ለምሳሌ የሄፓታይትስ መመርመሪያ ዘዴዎች ላይ በምርምር የማሻሻል ሥራ የተሰራ ቢሆንም፤ ወደ ኢንዱስትሪው በማስተላለፍ ወደ ምርት እንዲሸጋገር ያላደረገ እንዲሁም ከ12 መድኃኒት አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የራሳቸው የምርምር እና ልማት ክፍል ያላቸው ሶስት አምራች ኢንዱስትሪዎች ብቻ መሆናቸው፤

147. ከ12 የመድኃኒት አምራች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በማምረት ሂደት ላይ የሚገኙ 5 ፋብሪካዎች የመልካም አመራረት ስርዓት ያሟሉ ሲሆኑ 5ቱ አምራች የመልካም አመራረት ያላሟሉ በመሆናቸው ከየካቲት 08/2016 ዓ.ም ጀምሮ በሁለት ዓመት ተኩል የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቱን እንዲያሟሉ የጊዜ ገደብ የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እቅድ እና የአፈፃፀም ድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ክትትል እና ድጋፍ አለመደረጉ፤

148. ለምርምር ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት በትክክል ለታለመላቸው ዓላማ መዋሉን ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀማቸው ላይ ክትትልና ግምገማ ስለማድረግ እና ግብረ መልስ ስለመስጠቱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

149. የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ኢንስቲትዩቱ ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፤የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ የሚደረግበት ስርዓት የሌለ እንዲሁም የምርምር ሥራ የሚያከናውኑ ተመራማሪዎች አስቀድሞ የወሰዱትን የምርምር ኮንትራት ሳያጠናቅቁ ተጨማሪ ኮንትራት የሚሰጣቸው መሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

150. የምርምር ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት የተራዘሙ 5 የምርምር ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

151. ኢንስቲትዩቱ ለምርምር ሥራ ሲጠቀምባቸው የቆዩ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ ኬሚካሎች ሳይወገዱ በተለያዩ መጋዝኖች ውስጥ አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ቁሳቁሶች ጋር የተቀመጡ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

5. በብሔራዊ የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማዕከል የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር አፈፃፀምን በተመለከተ፤

152. ማዕከሉ ከ2012-2016 ዓ.ም በማይክሮቢያል ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ዘርፍ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ያገኘ ቢሆንም የምርምር ዉጤቶችን ምርትና ምርታማነት ትኩረት በማድረግ ወደ ተጠቃሚ ተደራሽ ያላደረጋቸው እና የአዕምሯዊ ንብረት መብት ያላስመዘገባቸው መሆኑ፤

153. ማዕከሉ እንደየሥራ ፀባዩ ለሰራተኞች የሚያስፈልገውን የሴፍቲ ዕቃዎች በሚፈለግበት ጊዜና መጠን ገዝቶ እንዲሰጣቸው የሰራተኛ የደንብ ልብስ መመሪያ የሚደነግግ ቢሆንም፤ ማዕከሉ ለባለሙያዎች የሚያሰፈልገውን የሴፍቲ ዕቃዎች ለሥራ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ጥራትና መጠን የማያቀርብ መሆኑ፤

154. በማዕከሉ የተከናወኑ የማይክሮቢያል፣ የእንሰሳትና የዕፅዋት ላብራቶሪዎች፣ የእንስሳት መጠለያ እና የመኖሪያ ቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች ብር **38,255,089.06** እ.አ.አ በነሀሴ (August) 07,2018 ተጀምሮ በ420 የሥራ ቀናት ውሰጥ እንዲጠናቀቅ ውል የተገባ ቢሆንም 574 ቀናትን በማሳለፍ ርክክብ ያደረገ እና ብር **1,902,552.12** የዋጋ ልዩነት ለሥራ ተቋራጩ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

155. በማዕከሉ ውስጥ ሲገነቡ የነበሩ የማይክሮቢያል፣የእንስሳትና የዕፅዋት ላብራቶሪዎችና የግንባታ ሥራዎች የጥራት ጉድለት ያለባቸው በመሆኑ ተቋሙን ለሌላ ወጪ እየዳረገ መሆኑ፤

156. ማዕከሉ ከ2010 ጀምሮ እስከ 2016 ዓ.ም ግንባታዎችን ለማስፈፀም የግንባታ ፕሮጀክት እቅድ ሳይኖረው፣ ግልፅ ጨረታን ሳያወጣ፣ የበላይ መሥሪያ ቤቱን እና የሚመለከታቸውን አካላት ሳያስፈቅድ ብር **7,871,002.51** ወጪ በማድረግ የተለያዩ ግንባታዎችን ያከናወነ መሆኑ፤

157. ማዕከሉ ለመደበኛ እና ለፕሮጀክቶች የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋል ሲገባ በተለያየ ጊዜያት ሰራተኞች በመደበኛ ስራቸውና በዓመት እረፍት ላይ እያሉ የውሎ አበል ተሰርቶላቸው የሚጠቀሙ፣ ለሌሎቹ ደግሞ ከማዕከሉ ወደ ሌላ ተቋም ለስልጠናና ለሌላ ስራ ሲሄዱ ከሁለቱም ተቋማት ከማዕከሉና ከሚሄዱበት ተቋማት) አበል

ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑ፣

158. በማዕከሉና በማዕከሉ ሥር ያሉ ለግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር የሚያገለግሉ ላብራቶሪዎችና መሳሪያዎች በየጊዜው በአግባቡ ስለመስራታቸው የሚያሳይ ልኬት/ካሊብሬሽን ተደርገው ሰርቲፍኬት የሚያስፈልግ ሲሆን በማይክሮቢያል ምርምር ክፍል በ2016 ዓ.ም ብቻ ካሊብሬት የተደረገ ቢሆንም በእፅዋት እና እንስሳት ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ዘርፎች ያሉ ላብራቶሪዎችና መሳሪያዎች ካሊብሬት ተደርገው የማያውቁ መሆኑ፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

6. <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አተገባበር እና ቁጥጥር ሥርዓት አፈፃፀም በተመለከተ</u>፣

159. በስራ ላይ የሚገኘውን የአካባቢ ፖሊሲ ሰነድ 1989 ዓ.ም ከፌዴራል እና ከክልል የዘርፍ መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና በአካባቢ ላይ ከሚሰሩ አጋር ድርጅቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያግዝ የአካባቢ ፖሊሲ ለማዘጋጀት በ2009 ዓ.ም የታቀደ ቢሆንም አዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመዘጋጀቱን/ማሻሻያ አለመደረጉ፣

160. በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ይሁንታ ፈቃድ ለተለያዩ ዘርፎች ባለሙያዎችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ የክፍያ ተመን የሌለው መሆኑ፣

161. የአካባቢ ልማቱ የሚያስከትለው ወጪ ከሚያስገኘው ጥቅም አንጻር የግምገማና ትንተና ሥርዓት ያልተዘረጋ እና በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች/ወጪዎች ጉዳት አድራሽ አካሎች የልማት ፕሮጀክቶች (ኢንዱስትሪዎች) የአየር፣ የውሃ፣ የድምጽ እና የአፈር ብክለት ወይም የኃይል ብክነት ካሳ ክፍያ እንዲከፍሉ የሚያስገድድ ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

162. ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ፈቃድ ወስዶ በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችና ድርጅቶች የሙያ ሥነ ምግባር መመሪያ የማይፈርሙ እና በፈቃድ አሰጣጥ ትግበራ ላይ የሚፈጠሩ/የተስተዋሉ ችግሮችን በማስጠናት የመፍትሔ እርምጃ ተግባራዊ አለማድረጉን፣ እንዲሁም የተሰጡት ፈቃዶች ሕግና ደንብን ተከትለው መከናወናቸውን፣ የሕዝብን ሞራል መብትና ጥቅም የሚያስጠብቁ መሆናቸውን የማያረጋግጥ፣ ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፣

163. ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የአካባቢ ይሁንታ ያገኙ ሁሉንም ፕሮጀክቶች በተጠናላቸው

የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ መሠረት እንዲሁም ባዘጋጁት የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እና አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎችንና በሀገራችን ጸድቀው በወጡ የአካባቢ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እየሰሩ /እየተገበሩ መሆኑን ለማረጋገጥ በዘርፉ ፈቃድ ባላቸው ገለልተኛ ባለሙያዎች አካባቢ ኦዲት እንዲካሄድባቸው ያላደረገ መሆኑ፤

7. **<u>በኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የምርምር፣ የስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ</u>፤**

164. ኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የውሃ ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች በዳሰሳ ጥናት ተለይተው እንዲያዙ ያላደረገ፣ በህብረተሰቡ ላይ ያለውን የውሃ ችግር ከመቅረፍ አንፃር የተሰራው የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ በሀገሪቱ ካለው የውሃ ችግር አንፃር አነስተኛ መሆኑ፣ የተሰሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፤

165. በ136.96 ሚሊዮን ብር ወጪ ዕርዳታ የተገነባው ህንፃ/ለቢሮ አገልግሎት፣ ለመማሪያ ክፍሎች፣ ለላብራቶሪ አገልግሎት በ2012 ዓ.ም ተጠናቆ ከነሙሉ ቁሳቁሱ የተሟላ ቢሆንም ህንፃው ርክክብ አለመደረጉ፣ ርክክብ ባለመደረጉ ምክንያት አገልግሎት ሳይጀምር ከ5 ዓመታት በላይ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰራው ህንፃ ተዘግቶ የተቀመጠና አገልግሎት ሳይሰጥ ወደ እርጅና እየሄደ መሆኑ እንዲሁም በህንፃው ውስጥ ያሉት ለስልጠና እና ለላብራቶሪ አገልግሎት ሊውሉ ታስበው የገቡ ቁሳቁሶች ያለአገልግሎት የተቀመጡ ከመሆናቸው ባሻገር አገልግሎት ሳይሰጡ ቴክኖሎጂው እያለፈባቸው መሆኑ፤

166. በኢንስቲትዩቱ በመገንባት ላይ ያለው ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪን ለመስራት ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም በብር 52,945,227.72 ውል የተገባ ቢሆንም የግንባታ ሂደቱ ከሐምሌ 2014 ጀምሮ መቋረጡ፤ የስፔሻላይዝድ ላብራቶሪ ግንባታ አለመጠናቀቅ በዋነኛነት ወደ ውጭ ሀገር በመላክ የሚደረግ የውሃ ምርመራን በማስቀረት እየወጣ ያለውን የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተግባር እንዳይሳካ ማድረጉ፤

167. ኢንስቲትዩቱ የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ፍተሻ የአገልግሎት ዋጋ የክፍያ ታሪፍ በማዘጋጀትና በማፀደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ያላደረገና ክፍያ እያስከፈለ አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ መሆኑ፤

168. በኢንስቲትዩቱ የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት የምርምር ስራን ቢያቆሙ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ የሚያደርጉበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ በተለያየ ምክንያት የጀመሩትን የምርምር

ስራ የሚያቋርጡ የዩኒቨርስቲ መምህራን ተመራማሪዎች የያዙትን ማስረጃዎችን በመረከብ ተመሳሳይ ሙያ ላይ ባሉ ባለሙያዎች ተክቶ የማሰራት ሁኔታ መኖሩ ቢገለጽም ስራውን ያቋረጠውን ተመራማሪ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

8. በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነት በተመለከተ፤

169. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችን፤ የአኗኗር ባሕሪያቸውንና የመኖሪያ ሥፍራቸውን መሰረት ያደረገ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዝርያዎች የቁጥጥሩና የቅነሳ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ፍኖተ ካርታ /Road Map/፤ የስርጭት መጠንን የሚያሳይ መረጃ የሌለው መሆኑ፤

170. በምዕራብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች ከ75,000 ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ የሚገመት ከስድስት ዓመታት በላይ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ስራዎች በመቋረጡ ምክንያት በቆላ ዝንቦች ዳግም የተወረረ መሆኑ፤ ኢንስትቲዩቱ አዲስ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ስራ የሚሠራባቸው መሬቶችን ያላስፋፋ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ተጠቂ የሆኑ ቆላማና ከፊል ቆላማ አካባቢዎችን ተደራሽ ያላደረገ እና የቁጥጥር ሽፋኑን ያላሳደገ መሆኑ፤

171. በ2016 በጀት ዓመት መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች 9,346 ካሬ ኪሎ ሜትር ለማከናወን አቅዶ 3,650 ካሬ ኪሎ ሜትር በማከናወን 39.1 ከመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት 15,871 ካ.ኪ.ሜ መሠረታዊ መረጃ እሰበስባለው ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 22.9 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

172. በ2016 በጀት ዓመት በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆችን በቁጥር 4000 ለመትከል አቅዶ ምንም የታርጌት ተከላ ያላከናወነ መሆኑ፣ መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል 1,500 ካ.ኪ.ሜ ለመርጨት አቅዶ ምንም ርጭት ያላከናወነ፤ እንዲሁም የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በ3,880,000 እንስሳት ጀርባ ላይ ለመቀባት አቅዶ 1,661,528 እንስሳት በመቀባት 43 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤

173. በ2015 ዓ.ም ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል10,500 ትራፖችን/ወጥመዶችን ለመትከል አቅዶ 5,956 በማከናወን 56.7 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም የቆላ ዝንቦችን የውስጥ አካል በመክፈት ጥናት (Dissection) በቁጥር 5,120 ለማከናወን አቅዶ 2,460 ዝንቦች

የውስጥ አካል በመክፈት 48 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤

174. በኢንስቲትዩቱ የገንዲ ፓራሳይት ማከሚያ መድኃኒቶች መላመድ ምክንያት እንስሳት ከገንዲ በሽታ እየዳኑ ባለመሆኑ አማራጭ መፍትሔ ጥናትና ምርምር አለማድረጉ፣ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናትና ምርምር ሥራ ያልሰራ መሆኑ፤

175. በኢንስቲትዩቱ መጋዝን፣ በአርባ ምንጭ እንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል እና በአሶሳ እንስሳት ጤና ማዕከል ብር 4,385,001.27 የሚያወጡ ኬሚካሎች ለተገዙት አላማ ሳይውሉ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው /Expired/ በመሆኑ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

176. የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን የወላይታ ዞን ውስጥ አንድ ቀበሌ ከብቶቻቸውን ኬሚካል ለማስቀባት /ለማስረጨት/ የመጡትን አርሶ አደር፤ አርብቶ አደር እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮችን ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ከብቶቻችንን ኬሚካል ከማስቀባት/ ከማስረጨት/ ውጭ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስለሚያደርሰው ጉዳት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዳልተሰጣቸው የገለጹ መሆኑ፤

177. በኢንስቲትዩቱ፤ በክልል፣ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የማይታወቅና የአሠራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

9. <u>በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት የሥራ አፈፃፀምን በተመለከተ</u>፤

178. በ2016 የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት ወደ 2738 የሚጠጋ መጠለያ ጣቢያዎች የውስጥ ተፈናቃዮች ብዛት 3,306,698 የነበሩ ሲሆን ነገር ግን የተመደበው የሰብአዊ ዕርዳታ እየቀረበላቸው አለመሆኑ፤

179. በ2016 የተረጂዎች ልየታ ጥናት መሰረት በሃገሪቱ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች ተረጂ ህፃናት ቁጥር 489,290 (ከአጠቃላይ ተረጂ 15 ፐርሰንት) የሚገኙ ቢሆንም የተጨማሪ አልሚ ምግብ (በቆሎና አኩሪ አተር ቅይጥ CSB (corn, soya & bean) ከአምስት አመት በታች ላሉ ህፃናት፣ ለአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች ብቻ መሰጠት የሚገባው ቢሆንም ለሁሉም ተረጂዎች ያለ ምንም ተጨማሪ መስፈርት እንዲሰጥ የተደረገና በአፋጣኝ እየተተካ አለመሆኑ፤

180. በናሙና ተመርጠው በታዩ መጠለያ ጣቢያዎች በሐረር (ሐማሬሳ)፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በታዩ ሁለት ወረዳዎች ያሉ 10 መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፣ ነብሰጡር እና አጥቢ እናቶች የተጨማሪ አልሚ ምግብ (CSB) ካገኙ ወይም ከተቋረጠባቸው ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑ፤ እንዲሁም በእነዚሁ መጠለያ ጣቢያዎች ውሃ መብራትና የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ለረጅም ጊዜ የተቋረጠ መሆኑ፤

181. በኮሚሽኑ እየተከናወኑ ያሉ የቀብሪዳሃር፣ የፍኖተሰላም እና የሆሳዕና የመጋዘን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት ባለመጠናቀቃቸው መንግሥትን ለተጨማሪ ብር **9,094,417,387.08** ወጪ የዳረገ መሆኑ፤

182. ኮሚሽኑ ባሉት መጋዘኖች ውስጥ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ አነስተኛ ክምችት (Minimum Stock) የሚያዝበት ስርዓት በኮሚሽኑም ሆነ በክልሎች ስለመዘርጋቱ እና ሥርዓቱ ተግባራዊ ስለመድረጉ መረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤

183. ኮሚሽኑ ለሰብአዊ ዕርዳታ የሚሆን ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በተለያየ ቦታ ካሉት መጋዘኖቹ ለክልሎች ከላከ በኋላ በትክክል ስለመድረሱና ለተረጂዎች ስለመከፋፈሉ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው በሐረር፣ በካራሚሌ እና ደደር ወረዳዎች ለእለት እርዳታ የሚላከው ድጋፍ ለተጠቃሚው ስለመድረሱ ተገቢ የክትትልና የድጋፍ ስራ አለመከናወኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

10. <u>የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት የመንገድ ትራፊክ ደህንነት እና የሦስተኛ ወገን የመድን ፈንድ አገልግሎት አፈፃፀም በተመለከተ</u>፤

184. በአገሪቱ ውስጥ ያሉት የተሽከርካሪ ብዛት ለማወቅ የተደራጀ ትክክለኛ መረጃ ባይኖርም ነገር ግን አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ እና ትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠይቆ በሰጡት ምላሽ 1.4 ሚሊዮን ተሽከርካሪ መኖሩንና ከዚህ ውስጥ 962 ሺህ ተሽከርካሪ (69%) ብቻ የመድን ሽፋን ያላቸው ሲሆን፣ 438,000 የመድን ሽፋን የሌላቸው መሆኑ፤

185. በሲዳማ ክልል ብቻ ካሉት 40 ሺህ ሞተር ሳይክሎች ሁሉም የመድን ሽፋን የሌላቸው እና 12 ሺህ ብቻ ህጋዊ መንጃ ፍቃድ ባላቸው ሰዎች የሚሽከረከሩ መሆኑ፣ እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ያሉ ሞተር ሳይክሎች በአብዛኛው በህገወጥ መንገድ የገቡ መሆኑን የክልሉ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮና ትራፊክ ፖሊስ የገለፁ ሲሆን ትክክለኛ

ብዛታቸውን ለመግለጽ የሚያስችል መረጃ የሌላቸው መሆኑ፤

186. አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ከጉምሩክ ኮሚሽንና ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በመተባበር በህገ ወጥ መንገድ የሚገቡ፣ ያለህጋዊ መንጃ ፍቃድ የሚያሽከረክሩ እና የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የሌላቸው ሞተር ሳይክሎች ላይ መፍትሄ ያልተወሰደ መሆኑ፤

187. በአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 ላይ በተደነገገው መሠረት የሶስተኛ ወገን መድን ባልተገባለት ወይም ባልታወቀ ተሽከሪካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው አስቸኳይ ህክምና እንዲያገኝ ማድረግ፣ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ እንዲከፈለው ማድረግ ወይንም በአደጋው ለሞተ ሰው ቤተሰብ አባላት ካሣ እንዲከፈለው ማድረግ ሲገባው የፌደራል መንገዶች፣ በክልል ደረጃ ወረዳን ከወረዳ ከሚያገናኛቸው መንገዶች ውጪ ያሉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና ግንባታቸው ተጠናቆ ርክክብ ባልተደረገ/ መንገዶች ላይ በሚያሽከረክሩ ተሽከሪካሪ ለሚከሰት የትራፊክ አደጋ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ማረጋገጫ ስለማይሰጥ ተጎጂው የጉዳት ካሣ እና ነፃ የ3ኛ ወገን አስቸኳይ ህክምና ተጠቃሚ አለመሆኑ፤

188. አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ለትራፊክ አደጋ ተጎጂዎች የሚፈፅማቸውን የካሳ ክፍያ ኃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት አደጋው እንደደረሰ ወዲያውኑ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ተመላሽ ሊያስደርግ የሚገባ ቢሆንም ገጭተው ባመለጡ እና የ3ኛ ወገን በሌላቸው ተሽከርካሪዎች ከ2005 እስከ 2016 በጀት ዓመት በደረሱት የትራፊክ አደጋ ለ555 ተጎጂዎች ብር **16,051,275.48** ክፍያ የፈፀመ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የ44 ተጎጂዎች ብር 1,937,857.30 የካሳ ክፍያ ብቻ ተመላሽ የተደረገ መሆኑ፤

189. በየዓመቱ የትራፊክ አደጋ ደርሶባቸዋል ተብሎ በጤና ሚኒስቴር የሚቀርቡ መረጃዎች ከፌዴራል ፖሊስ እና ከመንገድ መድህን ፈንድ አገልግሎት የተያዙት መረጃዎች የማይጣጣሙ እና የጤና ሚኒስቴር መረጃ ከሁለቱ ተቋማት ብልጫ የሚያሳይ መሆኑ፤

190. ከፌዴራል ፖሊስ የተመዘገበው ከ2014 እስከ 2016 ባላው ጊዜ ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ የትራፊክ አደጋ ብዛት 2136 ሲሆን የጉዳት ካሳ የተከፈላቸው ተጎጂዎች ብዛት 128(6%) ብቻ ሲሆን አገልግሎቱ የከፈለው የካሳ ክፍያ እና የተጎጂዎች መረጃ ብዛት ልዩነት ያለው በመሆኑ በአዋጁ መሠረት አብዛኛው ተጎጂዎች የጉዳት ካሣ ያልተከፈላቸው መሆኑ፤

191. በአሁኑ ወቀት እየተሰራበት ያለው የደኅንነት ቀበቶ መመሪያ ቁጥር 36/2012 የደህንነት ቀበቶ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች ነባር (በሥራ ላይ ያሉ) እስከ 150 / አንድ መቶ

ሀምሳ/ ኪሎ ሜትር የሚጓዙ ሚኒባሶች እና የህዝብ ማመላለሻዎች ከ5 እስከ 8 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች እና ረጅም ርቀት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖራቸውና ተሳፋሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚወስን ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

192. የፍጥነት መገደቢያ መመሪያ ቁጥር 27/2011 ማንኛውም የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጥም በመመሪያው ላይ የተካተቱና መሣሪያው ሣይገጥምላቸው በመንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከሉ ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት መሳሪያው ያልተገጠመላቸው መሆኑ፤

193. አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የፍጥነት መቆጣጠሪያ (Speed Break) የሚሠራበት ስታንዳርድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና፣ ለህብረተሰቡ ስለምልክቶቹ ግንዛቤ ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት እየተሰሩ ያሉ የፍጥነት መቆጣጠሪያ (Speed Break) በስታንዳርዱ መሰረት የተሽከርካሪውን ከፍታ ያልጠበቁ፣ ዜብራ ምልክቶች ያልተቀቡ እና የፍጥነት መቆጣጠሪያ (Speed Break) መኖሩን አመላካች ምልክቶች ያልተተከሉ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

11. <u>በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት የመማሪያ ማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅት፣ ህትመትና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ</u>፤

194. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በጥር 2014 ባጸደቀው የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት፣ ህትመት ስርጭትና አጠቃቀም ማንዋል አፈጻጸም መሰረት ያልተዘጋጁ የመማሪያ መጻሕፍት መኖራቸው፤

195. መጽሐፍት ጥምረት አንድ መጽሐፍ ለአንድ ተማሪ እንዲዳረስ ያለተደረገ መሆኑ፣ በናሙና ከታዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል 1 ለ19 የተማሪ - መጽሐፍት ጥመርታ እንዲሁም ከ9ኛ -12ኛ 1 ለ 5 የተማሪ -መጽሐፍት ጥመርታ ያለባቸው ትምህርት ቤቶች መኖራቸው፤

196. ለ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀት ለመጠየቅ ለገንዘብ ሚኒስቴር በፃፈው ደብዳቤ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ለ6,507,791 ተማሪዎች 79,360,795 የተማሪ መፃህፍት እና 164,695 የመምህር መምሪያ በድምሩ 79,525,490 መጽሐፍት የጠየቀ መሆኑን እና ከ2016-2017 ዓ.ም የታተሙት የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት እና የመምህር መምሪያ 39,556,703 (49.7 ፐርሰንት) ብቻ መፃህፍት መሆናቸው፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች በኩል መታተም የነበረባቸው ወደ ህትመት ያልገቡ የትምህርት አይነቶች

መጻህፍቶች መኖራቸው፣

197. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመማሪያ መጽሀፍት ሥርጭት የዓመቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ለትምህርት ቤቶች ደርሰው እንዲሰራጩ ያለተደረገ መሆኑ፣

198. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በ2015 ዓ.ም የጎልማሶች ሲለሸስ በማዘጋጀት ለክልሎች የላከ ቢሆንም ከኦሮሚያ ክልል ውጪ የጎልማሳ መሰረታዊ ትምህርት የሞጁል ህትመት ያከናወነ ክልል የሌለ መሆኑ፣ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ9-12ኛ ክፍል ላሉ ዓይነ ሥዉራን ተማሪዎችና አስተማሪዎች የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍትን ብሬይል ያላዘጋጀ መሆኑ፣

199. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ለመለየት የሚያስችል በቅድመ አንደኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ማንዋል በማዘጋጀት ለክልሎች በማሰራጨት በማንዋሉ አፈፃፀም ላይ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከተለዩ በኋላ በአካቶ ትምህርት ብቻ የሚማሩ መሆኑን በየትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን የሚያግዝ የአካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማዕከል የሌለ መሆኑ በተጨማሪም የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች ለማስተማር የሚያግዝ በረቂቅ የተዘጋጀውን ማንዋል ፀድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

12. <u>በጤና ሚኒስቴር የወባና የቲቢ ፈንድ አፈፃፀም ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፣</u>

200. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በወባ በሽታ የሚያዙ ሰዎች መጠን ለመቀነስ በስትራቴጂክ እቅድና በዓመታዊ እቅድ እያቀደ የሚሰራ ቢሆንም ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በወባ በሽታ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ የሄደ መሆኑ፣ ይህም በወባ በሽታ የተያዙ ሰዎች ቁጥር በ2014 ዓ.ም 1,612,218 ፣ በ2015 ዓ.ም 3,303,469 እንዲሁም በ2016 ዓ.ም 5,677,912 መሆኑ፣

201. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በወባ በሽታ የሚሞቱ ሰዎች መጠን ለመቀነስ በስትራቴጂክ እቅድና በዓመታዊ እቅድ እያቀደ የሚሰራ ቢሆንም በሀገር አቀፍ በወባ በሽታ የሞት መጠን በ2014 ዓ.ም 180፣ በ2015 ዓ.ም 296 እና በ2016 ዓ.ም 766 ሰዎች የሞቱ ሲሆን ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በወባ በሽታ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ የመጣ መሆኑ፣

202. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውነው የወባ በሽታ አምጭ የቬክተር ቁጥጥር ተግባራትን ለማጠናከር የታለመ የቤት ውስጥ እርጭት፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ የፀረ-

ተባይ መረቦች (አጎበር) ሽፋን ከወባ በሽታ ተጋላጭ ከሆኑ ማህበረሰቦች አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ፤ እንዲሁም ሁሉም የተሰራጩ አጎበሮች በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋሉ አለመሆኑ፤

203. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቲቢ በሽታ የሚያዙ እና የሚሞቱ ሰዎች መጠን ለመቀነስ ስትራቴጂክ እቅድና ዓመታዊ እቅድ እያቀደ የሚሰራ ቢሆንም በቲቢ በሽታ የሚያዙ እና የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር መቀነስ ያልቻለ መሆኑ፤

13. በሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ክትትል እና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በተመለከተ፤

204. የፕሮጀክቶች ፅንስ ሀሳቦች (Proposal) ከማዘጋጀቱ በፊት በየስራ ክፍሎቹ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች ዳሰሳ ጥናት (Human right gap Assessment) በማስራት ወቅቱን ያገናዘበ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች ለይቶ በቅደም ተከተል ተግባራዊ የማያደረግ መሆኑ እንዲሁም ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ሲቀርጽ በፕሮፖዛሉ የሚተገበሩ ተግባራቶች እንደ አማራጭ (Optional) የተቀመጡ መሆኑ፤

205. ኮሚሽኑ በገንዘብ ሚኒስቴር ከወጣው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ 413/2013 አንቀጽ 11.3 መሰረት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልግ ባለሙያ ሳይቀጥር ወይም ሳይመደብ ለቋሚ ሰራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም እና የጡረታ መዋጮ ከፕሮጀክት በጀት የሚጠቀም መሆኑ በዚህም በአጠቃላይ ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም ለቋሚ ሰራተኛ ብር **9,403,103.55** ከፕሮጀክቶች በጀት ያለአግባብ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

206. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 1224/2012 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የዋና ኮሚሽነር፣ የምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ሌሎች ኮሚሽነሮች ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅሞች በመንግስት ከፍተኛ ተሿሚዎች መሰረት ተፈጻሚ እንደሚደረግ የተገለጸ ቢሆንም ከግንቦት 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም ድረስ ባለው መከፈል የነበረበት ብር **1,018,190.00** ቢሆንም ብር **5,267,008** በመከፈሉ አለአግባብ ብር 4,248,818 የተከፈለ መሆኑ፤ በተጨማሪም ለቤት አበል (House allowance) በመመሪያው ከተቀመጠው በላይ በብልጫ ብር **211,500** የተከፈለ መሆኑ፣

207. በኮሚሽኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፈጣን ምላሽ የመረጃ ቋት ለማበልፀግ Ethiopian human rights commission addressing critical human rights concerns nationwide (EU-DIHR) ፕሮጀክት (ከህዳር 22/2015 - ግንቦት 23/2016 ዓ.ም) 20,000 ዩሮ የተመደበ ቢሆንም የመረጃ ቋቱ እንዲበልጽግ ያልተደረገ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

14. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ቅበላ፣ ክምችት እና የግብይት ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ፤

208. በኦዲቱ ናሙና ከታዩ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች በወቅቱ ባለመታደሱ የፈረሰ፣ ወለሉ የተሰነጠቀና አጥር የሌለው፣ የመጋዘኑ ዙሪያ ለጎርፍ የተጋለጠና ጣራው ዝናብ የሚያስገባ፣ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች ምርት የጫኑ መኪኖች ማቆሚያና የናሙና መውሰጃ ቦታ የሌላቸው ሲሆን በጥቅሉ ዘመናዊ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው በመሆናቸው የምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ያልሆኑ መሆኑ፤

209. ምርት ገበያው 25 የሚደርሱ የግብርና ምርቶች በጥናት ለይቶ የኮንትራት ሰነድ የተዘጋጀላቸው ቢሆንም ምርት ገበያው የሚቀበላቸው የምርት አይነቶች በናሙና በታዩ ቅርንጫፎች (ሳሪስ፣ አዳማ፣ ሀዋሳ፣ ዲላ፣ ጂማ እና ቦንጋ) ባሉ መጋዘኖች ውስን ምርቶችን ብቻ መሆናቸው፤ ለማሳያ (ለሀገር ውስጥ ግብይት የሚውል ቡና፣ የተለያዩ የቦሎቄ አይነቶች፣ ሰሊጥ፣ አረንጓዴ ማሾ፣ አኩሪ አተር) ብቻ ቅበላ እንደሚያደርጉ ታይቷል፡፡የምርት ቅበላ መጠኑም ከ2014-2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከ40,049 እስከ 294,805 ቶን ወይም ከ13 በመቶ እስከ 49 በመቶ እየቀነሰ የመጣ መሆኑ፤

210. ምርት ገበያው መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ አባላቱን ቁጥር በመጨመር የግብይት አድማሱን ከማስፋት ይልቅ አባላቱ ወደ ሌሎች አማራጭ የግብይት ሥርዓቶች በመሄድ ከ2014-2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በምርት ገበያው በተከናወኑ ግብይቶች የተገበያየ የምርት መጠን ከ 42,874 እስከ 314,446 ቶን ወይም ከ14 በመቶ እስከ 51 በመቶ የቀነሰበት ሲሆን ያገበያየው የገንዘብ መጠን ከብር 3,712 እስከ ብር 11,884 ሚሊዮን ወይም ከ13 በመቶ እስከ 30 በመቶ እየቀነሰ የመጣ መሆኑ፤

211. ከ2014-2016 ዓ.ም ባለው የግብይት ማስረጃ መሰረት ኤክስፖርት ስታንዳርድ የሆኑ የምርቶች መጠን ከ47,529.11 እስከ 59,813.58 ሜትሪክ ቶን ወይም ከ19 በመቶ እስከ 29 በመቶ የቀነሱ መሆኑ፤

212. ምርት ገበያው የሚያገበያያቸው የሀገር ውስጥ ፍጆታ ምርቶች ለህገወጥ/ኮንትሮባንድ ንግድ እንዳይጋለጡ እና መዳረሻቸው የት እንደሆነ ለማወቅ እንዲረዳው ሥራውን እንዲሰሩ ኃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት (ጉሙሩክ፣ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ፖሊስ…) ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ሥርዓት ዘርግቶ እየተከታተለ አለመሆኑ፤

213. ምርት ገበያው በየበጀት አመቱ በዉጭ ኦዲተሮች ኦዲት ማስደረግ ቢኖርበትም ከ2010 ዓ.ም በኋላ ኦዲት ያላስደረገ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

15. <u>የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የስራ አፈፃፀምን በተመለከተ</u>፤

214. ፌዴሬሽኑ ከአዲዳስ ስፖርት ካምፓኒ ጋር እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1/2013 እስከ 31 ዴሴምበር 2020 ድረስ የስፖንሰርሽፕ ስምምነት መሰረት በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ውድድሮች ላይ የአዲዳስ ካምፓኒን በአልባሳት ሊያስተዋውቅ ካምፓኒው ደግሞ የዶላር ገንዘብ እና የስፖርት ትጥቅ አቅርቦት ሊሰጥ ውል መግባቱና የተገባው ውል እስከ 31 ዴሴምበር 2024 የተራዘመ መሆኑ፤

215. በዚሁ በተፈረመው ውል አንቀጽ ሁለት ላይ ከአዲዳስ ካምፓኒ ለሚገቡ ትጥቆች ፌዴሬሽኑ የትራንዚትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ወጪ ሳያወጣባቸው (Free Charge) እንደሚያቀርብ የተጠቀሰ ቢሆንም ፌዴሬሽኑ ግን ከአዲዳስ ካምፓኒ ለመጡ ትጥቆች ለትራንዚትና መጋዘን ወጪ ከ2014 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም በድምሩ ለሶስት አመት በዉሉ ሳይካተት እና እቅድ ሳይያዝ ብር **3,588,096.78** መከፈሉ በኦዲቱ ተረጋግጥዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 1,835,882.41 ለምን ጉዳይ እንደተከፈለ ማስረጃው ስላልቀረበ የወጣው ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

216. በተጨማሪም 2015 እና 2016 ዓ.ም ከላይ ያሉት ወጪዎች በውጭ ኦዲት ሲያስመረምሩ በኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ በወጪ መልክ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

217. በየዓመቱ ከሚላኩት የስፖርት ትጥቆች መካከል አንደኛው ለስልጠና ፕሮጀክት ታዳጊ አትሌቶች (Youth Athletes) ሲሆን በየዓመቱ ለ1200 ታዳጊ አትሌቶች 11 የትጥቅ አይነቶች እንደሚላክ ውሉ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ፌዴሬሽኑ ለስልጠና ፕሮጀክት ለታዳጊ አትሌቶች የሚልከው የትጥቅ አይነትቶች 6 አይነቶች ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎቹ አምስት የትጥቅ አይነት ያልተላኩ መሆናቸው፤

218. የአትሌቶች የማበረታቻ ሽልማት ማስፈፀሚያ መመሪያ በፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ፊርማ የተረጋገጠ አለመሆኑ፣ በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ቃላቶች ተገቢዉን ትርጉም ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ መመሪያው በውጪ አገር ውድድር ለተሳተፉ አመራሮችና የፌዴሬሽኑ ሰራተኞች የሚፈቅደው የሽልማት መጠን ከአትሌቶች የሽልማት መጠን

የሚበልጥ መሆኑና ፍትሐዊነት የሚጎድለው መሆኑ፤

219. የፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት እውቅና እንደሚሰጥ ቢገለጽም ምን አይነት እውቅና እንደሚሰጥ የእውቅና አፈፃፀም ስትራቴጂ/የማስፈፀሚያ ሰነድ አለመኖሩ እንዲሁም ከመንግስት ለሽልማት የሚሰጥ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለተሸላሚዎች ያላስተላለፈ መሆኑ፤

220. ፌዴሬሽኑ ከአዲዳስ ካምፓኒ በገባው ውል መሰረት ከካምፓኒው በየዓመቱ የተላከለትን የዶላር ገንዘብ መጠን የሚያሳይ ከካምፓኒው የተላከ ማስረጃ እንዲሁም የዶላር ገንዘቡ የሚቀበልበት የውጭ ምንዛሪ አካውንቶች ብዛት ስንት እንደሆኑ እና የውጭ ምንዛሪ አካውንቶቹ ኦዲት የሚደረጉ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፤

221. ፌዴሬሽኑ በየዓመቱ የሚሰበስባቸውን ገቢዎችን በዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ የማይመዘገቡ መሆናቸው እና ለምን ዓላማ እንደዋሉ ያልታወቁ፤

222. እ.ኤ.አ በኦገስት 15/2022 በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር ወቅት ለተሳተፉ የቡድን አባላት ውድድሩ ከተጠናቀቀ በኋላ የተጨማሪ የአምስት ቀን አበል ያለአግባብ **በዶላር 20,450** ለቡድኑ ማበረታቻ ተብሎ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

223. በፌዴሬሽኑ 2014 ዓ.ም በተዘጋጀ የግዥና ፋይናንስ መመሪያ ውስጥ ባልተጠቀሰበት ሁኔታ የዶላር ገንዘብ ሽያጭ/ልውውጥ የሚካሄድ መሆኑ ማለትም የተለያዩ ግለሰቦች እና ተቋማት የዶላር ገንዘቡን በኢትዮጵያ ብር ለመቀየር በመስማማት የሚለዋወጡ ሲሆን የሚቀየረው የኢትዮጵያ ብርም በህጋዊ ደረሰኝ ወደ ፌዴሬሽኑ አካውንት ገቢ ስለመደረጉ ወይም በተሰብሳቢ መልክ ስለመያዙ የፌዴሬሽኑ ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም ያሉ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች የማያመላክቱ መሆናቸው እና አጠቃላይ ለግለሰቦችና ተቋማት በብር እንዲቀየር ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

16. <u>በስራና ክህሎት ሚኒስቴር የስራ ዕድል ፈጠራ እና የውጭ ሀገር ስራ ስምሪት አፈጻጸም በተመለከተ፤</u>

224. በ2016 በጀት ዓመት 478 አዳዲስ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለመክፈት ታቅዶ 77 ብቻ የተከፈተ መሆኑ፣ በዚህ መሰረት አዲስ አንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ያስከፈቱ ክልሎችን ስንመለከት አማራ ክልል 148 ታቅዶ 36፣ አፋር ክልል 5 ታቅዶ 9፣ ኦሮሚያ ክልል 298 ታቅዶ 20፣ ደቡብ ምዕራብ 6 ታቅዶ 4፣ ሶማሌ

15 ታቅዶ 7 እና ደቡብ ኢትዮጵያ 6 ታቅዶ 1 ማዕከላት የከፈቱ ሲሆን ከዕቅዳቸው አንጻር ከአፋር ክልል በቀር የሌሎቹ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ፤

225. ሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞችና ከስደት ተመላሽ ስራ ፈላጊ ዜጎች ቅድሚያ የስራ ዕድል ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ምቹ የሆነ የመስሪያ ቦታና የፋይናንስ ድጋፍ ያልተደረገ በመሆኑ አፈጻጸሙ በዕቅድ ከተያዘው ዝቅተኛ መሆኑ፤

226. በ2014 በጀት አመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ብር **23,578,975,963** ብድር ለኢንተርፕራይዞች ለማሰራጨት ታቅዶ ብር **9,519,130,935** (40%) የተሰራጨ መሆኑ፣ ይህም በመደበኛ የታቀደው **14,532,866,595** ሲሆን አፈጻጸሙ **6,061,874,701** (41%) መሆኑ እንዲሁም ተዘዋዋሪ (ከብድር ተመላሽ) የታቀደው 9,046,109,368 ውስጥ አፈጻጸሙ 3,457,256,234 (38.2%) ሲሆን በ2016 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ 48 ቢሊዮን ብር በብድር 261,382 ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 17.029 (35%) ቢሊዮን ብድር ለ 73,568 (28%) ኢንተርፕራይዞች የተሰራጨና አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

17.<u>በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የኪራይ ቤቶች አስተዳደር የሥራ አፈፃፀም በተመለከተ፤</u>

227. ኮርፖሬሽኑ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት የፌዴራል መንግስት ንብረት የሆኑ የኪራይ ቤቶችን በህግ አግባብ በመመዝገብ የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው ብቸኛ የፌዴራል ተቋም ቢሆንም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን በአሁኑ ስያሜው የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን (Ethiopia Mineral Corporation) ከህግ አግባብ ውጪ ተይዘው የሚተዳደሩና የሚከራዩ 36 ባለ G +1 ቤቶች እና 1 መጋዘንና 1 G+2 ህንፃ ያሉ ሲሆን የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በስሙ በተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ቤቶችን ለግለሰቦች እያከራየ ላለፉት 20 አመታት በላይ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ፣

228. ኮርፖሬሽኑ የንግድ ቤቶችን የኪራይ ማሻሻያ በማድረግ ገቢውን ያሳደገ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት ኪራይ ማሻሻያ ለማድረግ ረቂቅ ጥናት ያከናወነ ቢሆንም ለኮርፖሬሽኑ መመስረት ወይም ህልውና መሰረት ሆነው ያገለገሉ ቤቶችን ያበረከቱ የቀድሞ ባለንብረቶች ወይም አንጋፋና አረጋዊያን የሆኑ ዜጎች (Senior Citizens) ለኮርፖሬሽኑም ሆነ ለሀገር ያደረጉትን አስተዋፅዖና ሰብዓዊነትን ጭምር ታሳቢ ያደረገ የአበል ማሻሻያ ያልተደረገ መሆኑ፤

229. በኮርፖሬሽኑ ቤቶች የሚገለገሉ የተለያዩ የፌዴራል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት አስፈላጊውን የኪራይ ውል በመዋዋል ለኮርፖሬሽኑ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ክፍያ የማይከፍሉ መኖራቸው በዚሁ መሰረትም ከ10 ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ ያልተሰበሰበ በድምሩ ብር 29,349,812.40 መኖሩ፤

230. የኮርፖሬሽኑ የቤቶችና ይዞታዎች ማስከበርና ማከራየት ዳይሬክቶሬት ሰኔ 2016 ባደራጀው የቤት ጠያቂዎች ዝርዝር መረጃ መሰረት በቁጥር 136 የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እና የተለያዩ የፌዴራል ተቋማት በድምሩ 1809 (አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዘጠኝ) ለሚሆኑ ሰራተኞች እንዲሁም በድሬዳዋ ቅርንጫፍ 928 (ዘጠኝ መቶ ሀያ ስምንት) በአጠቃላይ 2,737 (ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት) የቤት አቅርቦት ጥያቄ ያቀረቡና ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

18. <u>የሁምቦ ጠበላ አባያ፣ የሀዌላ ቱላ ወተራሬሳ ያዬ ወራንቼ እና የቦኖሻ አጫሞ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ፤(በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተጠየቀ)</u>

231. አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ የሁምቦ ጠበላ አባያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በጨረታ ሂደት ወቅት የተጫራቾችን የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ብቃት /Qualification/ ምዘና በማድረግ ያላቸውን ቁልፍ የሰው ኃይል፣ የግንባታ ማቴሪያል፣ የፋይናንስ አቅም እና መልካም ስም ግምት ውስጥ ሳያስገባ ወደ ስራ መግባቱና የተጫራቾችን ዝቅተኛ ዋጋ /List Price/ እንደ ዋና መስፈርት ብቻ መጠቀሙ በፕሮጀክቶቹ የስራ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ መሆኑ፤

232. የሁምቦ ጠበላ አባያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ፣የቦኖሻ አጫሞ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት እና የሀዌላ ቱላ ወተራሬሳ ያዬ ወራንቼ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት፣ የፋይናንስና የማሽነሪዎች ብቃት የአቅም ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ ፕሮጀክቱን በተያዘለት ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉ፣ በኦዲቱ ወቅት የታዩ መሆኑ፤

233. የሁምቦ ጠበላ አባያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አማካሪ አርትስ ቴክ ፣ የሀዌላ ቱላ ወተራሬሳ ያዬ ወራንቼ አማካሪ ዩኒኮን እና የቦኖሻ አጫሞ አማካሪ ድርጅቶች በኮንትራት ስምምነቱ ውል ሲገቡ ያቀረቧቸውን እና ቁልፍ ባለሙያዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ፕሮጀክት ሳይት ያላሰማሩ መሆኑ፣ አማካሪ ድርጅቶቹ በኮንትራት ስምምነቱ ውል

ሲገቡ ያቀረባቸው ቁልፍ ባለሙያዎች ለጨረታ ማሸነፊያ ብቻ እየተጠቀሙባቸው እና ወደ ሳይት የማይመድቧቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤

234. አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው ጊዜ እና ገንዘብ/ በጀት እየተከናወኑ መሆኑን አማካሪ መሐንዲሱ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ በተገቢው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ አላደረገም፡፡ ለማሳያም፡-

235. የሁምቦ ጠበላ አባያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ለፕሮጀክቱ የተያዘዉ ብር 699,000,000.00 የቦኖሻ አጫሞ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት፣ በብር 682,155,064.23 ፣ የሀዌላ ቱላ ወተራሬሳ ያዬ ወራንቼ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በብር 1,829,883,516.96 ለያንዳንዱ ፕሮጀክት ውል ተፈርሞ ስራ ቢጀመርም ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸዉ ግዜ አለመጠናቃቸዉን በኦዲት ወቅት ታይተዋል።

236. ከላይ የተጠቀሱ ሁሉም ፕሮጀክቶች በቀረበው የእያንዳንዱ ጊዚያዊ የክፍያ ሰርተፊኬት (Interim Payment Certificate) መሰረት የዋጋ ማስተካከያ (Price Adjustment) ክፍያ የተፈፀመ እና የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ዝቅተኛ በመሆኑ ወደፊት ተጨማሪ ወጭ ያለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

237. አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው ጊዜ፣ ገንዘብ/በጀት እና ጥራት እንዲከናወኑ በመከታተል መንገዶች ለተፈለገው አላማ እንዲውሉ፣ በፕሮጀክቶች መዘግየት አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪዎች እንዳይወጡ፣ የማህበረሰቡን ቅሬታና እሮሮ እንዲፈቱ፣ እየተፈጠረ ያለውን የፕሮጀክቶች የማጠናቀቂያ ጊዜ መራዘም እንዲቀረፍ አሳስበናል፡፡

19.<u>በፌዴራል ህብረት ስራ ኮሚሽን የገበያ ትስስር እና የፋይናንስ አቅርቦት አፈፃፀም ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

238. ኮሚሽኑ ወጥ የሆነ የህብረት ስራ የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓትን ገንብቶ መጠቀም ያልቻለ መሆኑ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን አደራጅቶና ተንትኖ ለመያዝ በ2014 እና በ2015 በጀት አመታት ለመስራት ቢያቅዱም ያልተከናወነ መሆኑ፤

239. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ 2 ከተማ መስተዳደር (ድሬዳዋና አዲስ አበባ)፣ 5 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ሀረሪ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ) ኮሚሽኑ በአመት አንዴ በሚያዘጋጀው ባዛር ላይ እንዲሳተፉ ከማድረግ ውጪ የህብረት ስራ ማህበራት የአባላትን ምርት በመረከብ እሴት በመጨመር አባል ለሆኑባቸው ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን የማስረከብ

ወይም የተሻለ የገበያ መዳረሻ በማፈላለግ እንዲሸጥ በህብረት ስራ ኮሚሽኑ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ፤

240. ኮሚሽኑ ጠንካራ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር የሚደግፉ የህብረት ስራ ማህበራት ፌዴሬሽን፣ ባንክ/ ፈንድ፣ ኢንሹራንስና የህብረት ስራ ሊግ ማቋቋም አለመቻሉ፤ የሀገሪቱን የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ የሚመራ እና ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል፣ ለእድገት የሚሰራ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ እንዲቋቋም ተገቢውን ትኩረት አለማድረጉ፤

241. በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ 7 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም በፌዴራል ተቋማት የሰራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር የኅብረት ስራ ኮሚሽን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከፋይናንስ ተቋማት እና ከሌሎች ሕጋዊ ተቋማት ጋር የፋይናንስ ትስስር ፈጥረው የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤

242. በአምስት ዓመት እቅድ ዘመኑ ለሦስት አመት ለትግበራ ከታቀደው የተለያዩ የግብርና ምርቶች በማቅረብ $ **469,235,294** የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ክንውኑ $ 179,270,118 ዶላር በአራቱ አይነት የግብርና ምርቶች ማለትም (ቡና፣ የቅባት እህል፣ የጥራጥሬ እና ማር) ከእቅድ አንፃር 40% ሲከናወን ከዶላር ግኝት አንፃር 38% መሆኑ፤

243. ኮሚሽኑ በህብረት ስራ ማህበራት በኤክስፖርት ምርት ግብይት ወይም ንግድ የሚስተዋሉ ችግሮች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ግብይት ተዋንያን ጋር ምክክር በመድረግ የዘርፉን ተግዳሮቶች እንዲፈታ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

244. ከላይ የተገለጹትን ዋና ዋና ግኝቶች እና በሁሉም የክዋኔ ኦዲትና የአካባቢ ኦዲቶች በዝርዝር ለየተቋማቱ በተላኩ ሪፖርቶች የተመለከቱትን ግኝቶችን መሰረት በማድረግ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተቋማቱ የድርጊት መሐር ግብር በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

20. <u>ልዩ ኦዲት</u>

245. መ/ቤታችን በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት በርካታ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በዕቅድ 12 ተይዞ የነበረ ቢሆንም በርካታ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በመቅረባቸው የተወሰኑ ቅድሚያ በተሰጣቸው 15 ልዩ ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቆ ሪፖርታቸው ለሚመለከታው አካል ተልኳል፡፡ 5 ልዩ ኦዲቶች ኦዲታቸዉ በመሰራት ላይ ሲሆን ሲጠናቀቁ ለጠያቂው አካል የሚላኩ ይሆናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸም

1. <u>የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ</u>፤

246. መ/ቤታችን የዓላማ ተኮር ሥርዓት ግንባታ ተከትሎ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ስራን ቆጥሮ በመስጠት ሥራዎቹ እስከ ሠራተኛ ድረስ በማውረድ ካስኬድ ተደርጓል፡፡ የሰራተኛውን የስራ አፈፃፀም በተሻለ መለካት የሚችል የአፈፃፀም የስራ አመራር መሳሪያዎች (Performance Management & Appraisal) ተዘጋጅቷል፤ በተጨማሪም የተቋሙ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ውጤታማነት ለመለካት እንዲያስችል የአፈፃፀም አመልካቾች (key Performance Indicators) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት ስራዎቹ እየተከናወኑ ሲሆን የስራ አፈጻጸም ምዘናም ወቅቱን ጠብቆ በመሞላት ላይ ነዉ፡፡ አገልግሎት አሰጣጣችን ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

247. ከየካቲት/2016 እስከ ጥር/2017 በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤታችን የመጡ ወንድ 400 ሴት 152 በድምሩ 552 ተገልጋዮች ሁሉም ተገልጋዮች በአግባቡ ከመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡

248. ከስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር ጠንካራ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መረጃዎችን የመለዋወጥ እና የስምምነት ሰነድ የመፈራረም ስራ የተከናወነ ሲሆን፤ ለሁሉም ማኔጅመንት አባላት ከጸረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመሆን በመልካም ስነ-ምግባርና ግንባታ ሞራል እሴቶች ግንባታ ላይ እና ሙስና መከላከል እንዲሁም የተቋሙ የሙስና ተጋላጭነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

249. በተቋሙ ውስጥ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል ማንኛውም ሰው ጥቆማ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ የአስተያየትና ጥቆማ መቀበያ ሁለት ሳጥኖች በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ጥቆማዎችንና አስተያየቶች እንዲሰጥ

ለማስቻል የነፃ ጥሪ መቀበያ አገልግሎት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

250. በበጀት ዓመቱ የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ የዲስፕሊን ግድፈት የፈፀሙ ወንድ 5 ሴት 1 በድምር 6 ሰራተኞች ከ3 ቀን እስከ 15 ቀናት የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት እርምጃ የተወሰደባቸው 2 ሠራተኞች ደግሞ ከፈፀሙት ከባድ የዲስፕሊን ግድፈት አንፃር የሥራ ውላቸው በተቋሙ እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን፣ ከደረጃ እድገት፣ ከዝውውር ምደባ አፈፃፀም እና ከዲስፕሊን እርምጃ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያቀረቡ 16 ሰራተኞች ጉዳያቸው በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ በወቅቱ ምላሹ በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

2. **<u>ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ</u>፤**

251. እንደ ከዚህ በፊቱ ለአካል ጉዳተኛ ሠራተኞች፣ ለሴቶችና ለሌሎችም የተቀመጠውን አዎንታዊ ድጋፍ በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በትምህርትና ስልጠና ላይ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

252. በፋይናንስ እና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፣ ወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ወዘተ በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በኦዲቱ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዩት ተደርግዋል፡፡

253. ሴቶች ቁልፍ የማኔጅመንትና የአመራር ሰጪነት ደረጃዎች ላይ መድረስ እንዲችሉ በሁሉም አካባቢ ማብቃት እንዲቻል ድጋፍና ክትትል በማድረግ ሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት(ODWaCE) ከተባለ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር በተለያዩ ርዕሶች የስርዓተ-ፆታና ማሕበራዊ አካታችነት ለማጠናከር የሚያስችል ስልጠና፣ ለአመራሮችና ሠራተኞች ዓለም አቀፍ ፀረ-ፆታዊ ጥቃት ቀንና የአካል ጉዳተኞች ቀን ምክንያት በማድረግ በሴቶችና አካል ጉዳተኞች ዙሪያ የወጡ የሕግ ማዕቀፎች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

254. ከሁለት የግል የሕክምና ማዕከላት በተደረገ ድጋፍ መሠረት ፈቃደኛ ለሆኑ 40 ሴት አመራሮችና ሠራተኞች ነፃ የጡት የቅድመ-ካንሰር የማሞግራፊና አልተራሳውንድ የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርግዋል ፡፡

255. በሌላ በኩል በዚህም ዓመት ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወጣቶችና የህፃናት ቀን መደገፍ እንደዚሁም የኤች አይ. ቪ. ኤዲስ ቀናት በተለያዩ

ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች በተቋሙ ውስጥ ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም በየ2 ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የሴት ሠራተኞች ፎረም አባላት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

256. ማህበራዊ ሃላፊነትን ከመወጣት አንፃር መሥሪያ ቤታችን አካባቢ በሚገኝበት ወረዳ 9 ለሚገኙ ጧሪ የሌላቸው 100 አረጋውያን 160,200 ወጪ በማድረግ ከነሙሉ ቤተሰቦቻቸው ለመታከም የሚያስችል ዓመታዊ የጤና መድህን ሽፋን ወጪ መሸፈን ተችልዋል፡፡

257. የመ/ቤቱ የሠራተኞች ክበብ አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻልና ክበቡን በማገዝ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሠራተኛው የምግብ አገልግሎት እየቀረበ ሲሆን መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን ሠራተኛዉ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ለሠራተኞች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

258. በዚህ አመትም በግማሽ ክፍያ የትምህርት እድል ለ10 ሴት ሰራተኞች የትምህርት ዕድል የተመቻቸ ሲሆን ለመግቢያ ፈተና ማዘጋጃ የሚሆኑ መረጃዎች እና ጥያቄዎች እንዲያገኙና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

259. ሁሌም እንደሚደረገዉ በዚህ አመትም የኦዲተሮች የመስክ የሥራ ድልድል ሲደረግ ለሴት ኦዲተሮች ቅድሚያ በመስጠትና ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ ስምሪት ድልድል ወቅት ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

260. በመሥሪያ ቤቱ የህጻናት ማቆያ በዓመቱ ውስጥ ወንድ 8 ሴት 6 በድምሩ ለ14 ሕፃናት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አገልግሎት በመስጠት እንክብካቤ የተደረገ ሲሆን፣ የሕፃናት ክፍሉም እንደ አዲስ የማደራጀትና ምቹ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ሌሎች 4 ወንዶች እና 2 ሴቶች በድምሩ 6 ሕፃናት የሕፃናት የቆይታ ግዜያቸውን አጠናቀው ወጥተዋል፡፡

3. <u>የአቅም ግንባታ እና ከኦዲት ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ</u>፤

261. በ2016 ዓ.ም 72 ዓይነት የሥልጠና ፍላጎቶችን በመለየት በማኔጅመንት በማጸደቅ የሥልጠና ካላንደር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፤ በፀደቀው ካላንደር መሰረትም ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

262. በዚሁ መሰረትም ለፋይናንስና ህጋዊነት እና ለክዋኔ ኦዲት 472 (305 ወንዶች እና 167 ሴቶች) የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ወንድ 147 እና ለ93

ሴት በድምሩ 240 ሰራተኞች በ4 የስልጠና ጉዳች ላይ የውጭ አገር በቨርቹዋል እንዲሁም 6 ሰራተኞች ውጪ አገር በአካል ስልጠና ያገኙ ናቸው፡፡

263. የድጋፍ አገልግሎት በ6 የስልጠና ርዕሶች ላይ 170 ወንድ እና ለ104 ሴት በድምሩ 277 ሰራተኞች ስልጠና ያገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በቨርቹዋል (Zoom) 130 ሠራተኞች ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

264. በሌላ በኩል ለ18 የመ/ቤቱ ሠራተኞች የትምህርት ዕድሎች የተሰጠ ሲሆን በዚሁም መሠረት ሁለተኛ ዲግሪ አገር ውስጥ 1 ሴት፣ ኤሲሲኤ (ACCA) ትምህርት 6 እንዲሁም በተጨማሪም IDI (INTOSAI Development Initiative) በሚሰጠው Professional Education for SAI (PESAI-P) የአንድ ዓመት ትምህርት በኦን ላይን (online) 10 ወንድና 1 ሴት ሠራተኞች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

265. የክልል እና የከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮችንና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ሙያዊ አቅማቸውን ለማጠናከር በ14 የተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ በፋይናንስና ህጋዊናት ኦዲት እና በክዋኔ ኦዲት ለ229 ሴት እና ለ645 ወንድ በድምሩ 874 ሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

266. በመ/ቤታችን አስተባባሪነትና የአፍሪካ እንግሊዘኛ ተናጋሪዎች የዋና ኦዲት ማህበር (አፍሮሳይ-ኢ) አዘጋጅነት የፋይናንሻል እና የህጋዊነት ኦዲት ማንዋሎች ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን አስመልከቶ በአዲስ አበባ በተዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ 3 ሴቶችና 1 ወንድ በድምሩ አራት አሰልጣኞች ጨምሮ ከ10 የተለያዩ የአፍሪካ አገራት የተወጣጡ 8 ወንድ እና 8 ሴት በድምሩ 16 ተሳትፈዋል፡፡ ከመ/ቤታችንም ዕድሉን በመጠቀም በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ 10 የሥራ ኃላፊዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ይህ ወርክሾፕ በሌላ አገር ቢዘጋጅ ኖሮ የተቋማችንን 10 ባለሙያዎች ለማሳተፍ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከመዳኑም በተጨማሪ ለአገራችንም የዉጭ ምንዘሬ ማስገኘት ተችሏል፡፡ አዳዲስ የተሰሩ የልማት ስራዎችን እንዲጎበኙ ተደርጓል፡፡

267. በተጨማሪም በAFROSAI-E አዘጋጅነት በየአመቱ የሚካሄደዉን 23ኛዉን የገቨርኒግ ቦርድ እና የስትራቴጂክ ሪቪው ስብሰባ ኢትዮጵያ በ2027 ለማስተናገድ ያቀረብነዉ ጥያቄ በሜይ 2025 ሲሸልስ ላይ በተረገዉ 21ናው ጉባዔ ላይ ተቀባይነት አግኝቶ ጸድቋል፡፡ ይህ ጉባኤ ሲካሄድም ለሀገራችን የዉጭ ምንዛሬ የምናገኝበት እንዲሁም አገራችንን የምናስተዋዉቅበት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

4. የኦዲት ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ እና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ፤

268. በአለታዊና ሳምንታዊ ጋዜጦች እንዲሁም በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ላይ የሚዲያ ዳሰሳ በማድረግ በአመቱ የመ/ቤቱን ስራ የሚመለከቱ 38 በተለያዩ ጋዜጦች የወጡ ዘገባዎችን እና 4 ሌሎች የድምጽና የምስል መረጃዎችን በማውጣት የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፤

269. የመ/ቤቱን 80ኛ አመት ምስረታ ለማሰብና የህንጻ እድሳት ስራውን ለማስመረቅ ለዉጭ ባለድርሻ አካላትና ለከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች እንዲሁም ለመ/ቤቱ ሠራተኞች በሁለት ዙሮች የተዘጋጀውን መርሀ ግብር መድረክ የማስተባበር እንዲሁም የመድረክና የአዳራሽ ዝግጅቶችን የማዘጋጀትና የማደራጀት እንዲሁም አዲሱን የመ/ቤቱን ተቋማዊ ብራንድና ሎጎ የሚያስተዋውቁ የተለያዩ በርካታ የህትመት ውጤቶችን ጨምሮ በቁጥር 300 የሚሆኑ ልዩ መጽሔቶችን በማዘጋጀት የማሳተም ስራዎች ተከናውነዋል፤

270. ቋሚ ኮሚቴዉ በሚያዘጋቸዉ ይፋዊ ህዝባዊ ስብሰባ 20 እና በመስክ ጉብኝቶች 15 በድምሩ 35 መድረኮች ላይ በመገኘት በተነሱ ጉዳዮች ላይ ተገቢ ማስረጃ በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በመ/ቤቱ የተሰጡ የግንዘቤ ማስጨበጫዎች፣ ይፋዊ የዉይይት መድረኮች፣ በአመቱ የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸው በድምሩ ከ102 በላይ የሚሆኑ ዜናዎችን፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፎችን እና ልዩ ልዩ መልእክቶችን የያዙ መረጃዎችን እንደየስርጭት አግባባቸው በመ/ቤቱ ድረ ገጽ፣ የፌስ ቡክ፣ የቴሌግራም፣ የሊንክዲን፣ የኢንስታግራም እና የቲውተር ገጾች የማሰራጨት ስራ ተከናውኗል፤

5. ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር አንጻር፤

271. መ/ቤታችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርግ በመሆኑ በርካታ ባለሙያዎችን ተግባራቸውን በየተቋማቱ በትራንስፖርት እየተንቀሳቀሱ የሚፈፅሙ በመሆኑ የመስክ እንቅስቃሴውን ውጤታማ ስምሪት በመስጠት ኦዲቱ በታቀደለት ጊዜ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

272. የመ/ቤታችንን የስራ አካባቢ የተሻለና የቢሮ ቅርጹንም መ/ቤቱ ከደረሰበት ዘመናዊ አሠራር ጋር የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ በፕሮጀክት ዕቅድ ተይዞ በበጀት ዓመቱ የህንጻ እድሳት ስራ ተጠናቆ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ በአዲስ በማሟላት የስራ አካባቢው ምቹ እና ማራኪ ማድረግ ተችሏል፡፡

6. የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ፤

273. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 669፣ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 344 እና 5 የበላይ አመራር በድምሩ 1018 የሰው ኃይል በ5 ዓመቱ የስትራቴጂክ እቅድ ዘመን የሚሟላ ተፈቅዷል፡፡ የኦዲት ሥራው በየካቲት ወር 2016 ሲጀመር 459 ኦዲተሮችና 196 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 655 ሠራተኞች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ በድምሩ 86 ኦዲተሮች እና ድጋፍ ዘርፍ 5 በድምሩ 91 ሠራተኞች ተቀጥረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በገዛ ፍቃዳቸው ስራ የለቀቁት ከኦዲት 19 ከድጋፍ 8 በድምሩ 27 ሰራተኞች እንዲሁም በጡረታ 8፣ በሹመት 1፣ በዲስፒሊን 1 በአጠቃላይ 37 ሰራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

274. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በግንቦት 30/2017 በመ/ቤቱ 522 የኦዲት ባለሙያዎች (361 ወንዶችና 161 ሴቶች)፣ 187 የድጋፍ ሰጪ (87 ወንዶችና 100 ሴቶች) ሠራተኞች 3 የበላይ ኃላፊዎች በአጠቃላይ 712 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት እና የውሎ አበል አነስተኛ መሆን ምክንያት ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

7. የ2016 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም፤

275. ለ2016 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር 192,459,038.00 ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ውስጥ ብር 188,509,385.89 (97.95%) መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለም/ቤቱ ተልኳል፡፡

8. የ2017 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም፤

276. ለ2017 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱ ስራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር **248,303,900.73** የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመጠቀም የታቀደው ብር **148,185,950.**00 ሲሆን በዕቅዱ መሰረት ብር **148,185,950.00** (100%) መጠቀም ተችሏል፤

9. የህንጻ ዕድሳት ፕሮጀክትን በተመለከተ፤

277. የህንጻው ክፍል ዕድሳት ተጠናቆ እና ሙሉ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ በአዲስ መልክ ተሟልቶ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን፣ ለህንፃ ዕድሳት ሥራው ማጠናቀቂያ በጀት ለ2017 በጀት ዓመት መደበኛ ካፒታል ብር **127,826,713.14** የተፈቀደ ሲሆን ብር **127,826,713.14** ለመጠቀም ታቅዶ አጠቃቀሙ ብር **127,826,713.14** (100%) መክፈል

ተችሏል፡፡ በዕድሳቱ ምክንያት ሌላ ቢሮ ሳንከራይ በመስራታችን ለኪራይ የሚወጣውን ብር 76,000,000.00 የሚሆን ወጪ ማዳን ተችሏል፡፡

10. **የአይፒኤፍ ፕሮጀክት፤**

278. መ/ቤታችን ከዓለም ባንክ ጋር በገባው ስምምነት መሠረት ለሚያከናውናቸው ኦዲቶች ለ2017 በጀት ዓመት በአይፒኤፍ (IPF) ፕሮጀክት በጀት ጥያቄ አቅርቦ በተፈቀደው በጀት አማካይነት የተለያዩ ግዥዎችን እና አገልግሎቶችን ለመፈፀም ከሀምሌ 2016 ብር 5,898,591.47 ወደ መ/ቤቱ አካዉንት የተላለፈ ሲሆን ብር 5,898,591.47 በመጠቀም አፈጻጸሙ 100% ሥራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

11. **የHuman Capital Operation (HCO) ፕሮጀክትን በተመለከተ፤**

279. ተቋሙ ለሚያከነዉናቸዉ ኦዲት ስራዎች ለማገዝ Human Capital ፕሮጀክት ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ጋር በገባዉ ስምምነት መሰረት ተቋሙ ለሚያከናዉናቸዉ ኦዲት ስራዎች በተለይም በአቅም ግንባታና የአይቲ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላትና በአጠቃላይ የተቋሙን ስራ ለመደገፍ ዉል ተገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት ከሀምሌ 01/2016 እስከ መጋቢት 30/2017 ዓ.ም ወደ አካዉንታችን የገባ ብር 19,300,000.00 ሲሆን አፈጻጸሙ 18,106,236.2 (93.8%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

12. **አገልግሎት የማይሰጡ ንብረት አወጋገድ በተመለከተ፤**

280. የቢሮ ፈርኒቸሮች፣ የተነቃቀሉ በሮች፤ ብረታ ብረቶች፤ የሽንት ቤት እቃዎች፤ የተለያዩ የቢሮ ቁሳቁሶች በመመሪያዉ መሠረት ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችና ለመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች በስጦታ በመስጠት እንዲወገዱ የተደረገ ሲሆን፣ በቁጥር 2 ሊፍቶችን በመመሪያው መሠረት በመንግስት ግዥ አገልግሎት አማካይነት ጨረታ ወጥቶ እንዲሸጡ ተደርጎ የሽያጩን ብር 725,525.00 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በማድረግ የመንግሥት ንብረት በአግባቡ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡

13. **ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተመለከተ፤**

281. በህንጻዉ እያንዳንዱ ወለል ላይ በጠቅላላ 9 ቴሌቪዥኖችን በመስቀል መረጃዎችን ማስተላለፍ እንዲችሉ የማድረግ ስራ የ11 ክፍሎችን የኦዲዮ ቪዠዋል ስርዓት ፕሮጀክት ዝርጋታ በማከናወን፣ የተቋሙ መረጃዎች ላይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎች ለመጠበቅ የሚያስችል ተግባራዊ የተደረጉ ሁለት የመረጃ ድንገተኛ አደጋ መጠበቂያ ስርአቶች (Data Recovery Back up system) ማለትም የመረጃ ግልባጭ ማስቀመጫን (Networker Backup)፤ የመረጃ ሰርቨሩን ደህንነት መጠበቂያ እና ወደ Cloud ግልባጭ

እንዲወስድ ወደተመደበለት ማስቀመጫ ቦታ ግልባጭ በማስቀመጥ ደህንነቱን የመጠበቅ ስራ ተከናውኗል።

282. የመ/ቤቱ ሥራዎች በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የኦዲት አሠራር የሚያዘምኑና የመ/ቤቱን የመረጃ ስርዓቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የመ/ቤቱን ሥራ ከማቀላጠፍ፣ ወረቀት አልባ ተቋም ለማድረግና ባለፉት አመታት ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የኦዲቱን ስራ በሲስተም በማገዝ ምቹ እና ቀላል ለማድረግ ስራዎቻችንን በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

14. <u>**መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች**</u>፤

283. በአበልና ጥቅማ ጥቅም ማነስ ምክንያት በርካታ ልምድ ያላቸው ሰራተኞችን ማቆየት አለመቻል፣

284. በአገሪቱ በተወሰኑ አካባቢዎች በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የኦዲቱ ሥራ ላይ በዕቅዱ መሠረት ማከናወን አለመቻል፣

285. የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመቀያየር ምክንያት መረጃን በጊዜ ማቅረብ አለመቻል፣

286. ከወቅቱ የኑሮ ውድነት አኳያ ለኦዲተሮች ለመስክ ሥራ ቆይታ የሚከፈለው አበል በቂ ባለመሆኑ በኦዲተሮች ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

15. <u>**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**</u>፤

287. የሰው ኃይሉን ለማቆየት የማቆያ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና የጎደለውን የሰው ኃይሉን በቅጥር ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፣ ቢሮና የሂሳብ ሰነዶች ችግር በተመለከተ ከኦዲት ተደራጊዎች ከየተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገርና ችግሩን እንዲያውቁት በማድረግ የሂሳብ ሰነዶችን በተጠየቀ ጊዜ እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ በስልክና በአካል በመወያየት ሰነዶችን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የፀጥታ ችግር በታየባቸው አካባቢዎች ሥራዎችን ለጊዜው በማቋረጥ በሌላ አካባቢ ኦዲቱን መሥራት የተቻለ ሲሆን፣ የፀጥታ ሁኔታ ማሻሻል የታየባቸው አካባቢዎችን እንደገና ኦዲቱን ማስቀጠል ተችሏል፣ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች በመግቢያ ስብሳባዎች ላይ ተገኝተዉ በጋራ በመወያየት ስለ ኦዲቱ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ በማስቻል በኦዲት ግኝቶች ላይም መፍትሄ በመፈለግ ረገድ ጥረት እንዲያደርጉና እንዲፈቱ የተደረገ ሲሆን፣ የመስክ አበልን በተመለከተ ከኑሮ ውድነቱ አንጻር ችግሩን ከግንዛቤ በመውሰድና ለችግሩም ትኩረት በመስጠት ለማሻሻል የመነሻ ሃሳብ ለኦዲት ኮሚሽን ቀርቦ በኦዲት ኮሚሽን በኩል

ለውሳኔ ለተከበረው ምክር ቤት ቀርቦ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡ የተከበረዉ ም/ቤት ጉዳዩን በአንክሮ አይቶ ምላሽ እንዲሰጠበት በአክብሮት እጠይቃለሁ

16. **የ2017/18 የኦዲት በጀት ዓመት ዕቅድ፤**

288. በአገሪቷ ለ2017 በጀት ዓመት ከተመደበላቸው 184 የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 13 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ፣ 1 የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ደግሞ ምክር ቤት በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ኦዲት እንደሚደረግ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 170 መ/ቤቶች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም ክዋኔ ኦዲት ደግሞ 32 አዳዲስ ኦዲቶችን እና 12 ክትትል ኦዲቶችን እንዲሁም 2 የኢንፎርሜሽን ሲስተም ሰርቪስ ኦዲት በድምሩ የ46 ኦዲቶች ሪፖርቶችን ለማውጣት በተጨማሪም የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች 316 የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን፣ 8 የማረጋገጥ ስራዎች (Verifications) ለመሥራት፣ 1 ፕሮግራም አቀፍ ማጠቃለያ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለመሥራት፣ 3 ልዩ ኦዲቶች እና 77 የዓመታዊ ግብዓት በድምሩ 405 ኦዲቶችን ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

17. **በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት፤**

289. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የእርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች እና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

290. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2016 በተከናወኑና ለመ/ቤታችን የደረሱ ኦዲቶች ላይ የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

291. በዚህ መሰረትም ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና

የተቋቋሙ ድርጅቶች 54 (የተለያዩ ዓመታት በጀት ዓመት ሪፖርትን በመቁጠር) ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 106 በድምሩ 160 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት እያንዳንዱን ሪፖርት በመቁጠር የተወሰዱ) ናቸው፡፡

292. ለመ/ቤታችን የደረሱት የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተኑ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 65፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 80፣ አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው (Disclaimer) 2፣ የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse Openion) 13 በድምሩ 160 ናቸው፡፡

18. <u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ</u>፤

293. ኮርፖሬሽኑ በ2016 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር **106,996,985** ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር **140,690,625** ገቢ ያገኘ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር **89,923,854** ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር **71,354,844** ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር **69,335,782** የተጣራ ትርፍ (ከታክስ በፊት) ሊያገኝ ችሏል፡፡

19. <u>ማጠቃለያ</u>

294. የ2016 በጀት አመት ሂሳብ ላይ የተካሄደዉ የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ በወቅታዊ ሁኔታ ከተቋረጡት ስድስት መ/ቤቶች በስተቀር በተቀሩት የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲቱ ተከናዉኗል፤ አፈጻጸሙም 96.7% ነው፡፡

295. በሌላ በኩል የክዋኔ ኦዲት እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 32 አዲስ፣ 8 የክትትል ኦዲት በድምሩ 40 ለመስራት ታቅዶ፤ የ31 ኣዳዲስ እና 8 የክትትል ኦዲት በድምሩ የ39 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ በመደረጉ አፈጻጸሙ 97.5% ሆኗል፡፡

296. የ2016 በጀት አመት የኦዲት ዉጤት ሲታይ ነቀፌታ የሌበት 115፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነዉ የተገኙ 38 እና የጎላ ችግር ያለባቸዉ ሆነው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው 10 ሲሆኑ በዚህ ዓመት የኦዲት አስተያየቶች ላይ መሻሻል ታይቷል፡፡

297. ከላይ መሻሻል ቢታይም በ2016 በጀት ዓመት የቀጠሉ እና ከዚያ በፊት ባሉ ዓመታት ይሻሻሉ ብለን አስተያየት ከሰጠንባቸው ውስጥ በዚህ ዓመትም የቀጠሉት የጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ፣ተሰብሳቢ ሒሳብ በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመከፈል፣ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠበት ገንዘብ በበቂ ሁኔታ አለመመለስ፣ ደጋፊ ሰነድ እንዲቀርብላቸው አስተያየት የተሰጠባቸው ሰነድ አለማቅረብ፣ በጊዜ ገደባቸው ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች መኖር፣ በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ገቢ አለመሰብሰብ ፣ደንብ እና መመሪያዎች ያልጠበቁ ግዢዎች፣ የበጀት አጠቃቀም ችግር፣ በብልጫ የተከፈለ ክፍያዎች፣ የመንግስት ንብረት አጠቃቀም እና አስተዳደር ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

298. በበጀት አመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረጉ የክዋኔ ኦዲቶች ለፕሮጀክቶች የቅድመ አዋጭነትና የዲዛይን ስራ አለመከናወን፣ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ በወቅቱ አለመጠናቀቅ፣ ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች ሊዘረጉ የሚገቡ የአሰራር ስርዓቶች አለመዘርጋት፣ የየመ/ቤቶቹን ቅልጥፍና እና ዉጤታማነት እንዲሁም ለተልእኮ ስኬት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የህግ ማዕቀፎችና ፖሊሲዎች አለመቀረጽ፣ የተቀረፁትም በተሟላ ሁኔታ አለመተግበር ዋና ዋና ግድፈቶች ሆነው ተገኝቷል፡፡

299. በዚሁ መሰረትም የፋይናንስና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት በተደረጉ ተቋማት በተላኩ ሁሉም ሪፖርቶች ላይ ጉድለቶችን ከማሳየት ባሻገር የታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለማረም እና ለማስተካከል የሚያስቸሉ የመፍተሄ ሃሳቦችን ጭምር ያካተቱ ከመሆኑም በላይ አብዛኛዎቹ የተሰጡት ማሻሻያ ሃሳቦች በኦዲት ተደራጊዎችም ጭምር ስምምነት የተደረሰባቸዉ ናቸዉ፡፡

300. ስለዚህ የሪፖርቱ አጠቃላይ ዘገባ ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች የ163 መ/ቤቶች የፋይናንሺያልና ሕጋዊነት ኦዲቶች፣ እንዲሁም 31 አዳዲስ እና 8 ክትትል በድምሩ 39 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራጅተዉ በሶፍት ኮፒ ለተከበሩ አፈጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን የም/ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተዉ እና ተመርምረው ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል እና ግፊት እንዲደረግበት በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

301. የተጠያቂነትን ስርዓት ከማረጋገጥ አንጻር፡ የመንግሰት ወጪ አሰተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም የጀመረዉን ግልጽ ይፋዊ መድረክ አጠናከሮ እዲቀጥልበት በአክብሮት እየጠየኩ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ፍትሕ ሚኒስቴር እና ሌሎች ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ ተቋማት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ የጀመሩትን እርምጃ

ተጠናክሮ እንዲቀጥል በዚሁ አጋጣሚ መልእክቴን ላስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

302. የነበረውን የኑሮ ውድነትና ጫና እንዲሁም ሌሎች ውጣ ውረዶችን በመቋቋም ያቀድነው እቅድ እንዲሳካ ጥረት ያደረጋችሁ በየደረጃው ያላችሁ የመ/ቤታችን ሰራተኞች በተከበረው ምክር ቤት ፊት አመሰግናለሁ፡፡

ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡